ሰባት ቤት ጉራጌ

የአንድ ብዙ ፍሬዎች

በሰባት ቤት ጉራጌ የጉመር ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በመጋቢት ወር በ1941 ዓ.ም. አቶ ገ/ማርያም ሞሞቼ በተባሉ አባት አማካይነት ነው። እኒህ ሰው በመጀመሪያ የአካባቢውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዲቁና የሚያገለግሉ ሰው ነበሩ። እውነትን ለመፈለግ ከነበራቸው ጥማት የተነሳ የወንጌልን ቃል ለመስማትና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በመፈጸም ረገድ ከፍተኛ ጉጉትና ጥማት ስለነበራቸው በአካባቢው የኦርቶዶክስ አማንያንና ካህናት ዘንድ እጅግ የተከበሩ ሰው ነበሩ። ይህም ብቻ አይደለም አብዛኛው የአካባቢው ሕዝብ የጣያቄ፡ አምልኮ ተከታይ ስለነበረ በአቶ ገብረ ማርያም የኦርቶዶክስ እምነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ተፈጥሮ በአካባቢው የነግ ባላባት በነበሩት አዝማች አስተባባሪነት የክርስትና እምነታቸውን ጥለው ወደ ባህላዊው የጣያቄ አምልኮ እንዲመለሱ በመከራ የታጀበ ስቃይ ሁሉ ደርሶባቸው ነበር።

---

[174] ከጊኒር ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተሠጠ የጽሑፍ ምንጭነት 1989 ዓ.ም.

በተለይም በ1939 ዓ.ም. ላይ የአካባቢው የጎሣ መሪ የነበሩትን ሰው አቶ ገብረ ማርያም እኔ ክርስቲያን ነኝ ወደ ጣዖት አምልኮ አልመለስም ብለው ስለቱገዳደሯቸው በሕዝብ ፊት አርባ ጅራፍ እንዲገረፉ አስደርገዋቸዋል። ይህ የወንጌል እውነት ጥማትና የእውነት ፍለጋ መሻት በአቶ ገብረ ማርያም ልብ እየተቀጣጠለ በመሄዱ የአምልኮ ነፃነት ፍለጋ ባለቤታቸውን ወ/ሮ ወ/ሚካኤል ማኒን እዚያው በቀኤቸው ትተው እርሳቸው ወደ አዲስ አበባ ይኮበልላሉ። አዲስ አበባ እንደደረሱ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ሲያሳድዱቸው ከነበሩት የአካባቢው የጎሣ መሪ ከአዝማች ሺፋ ጋር ይገናኛሉ። አዝማች ሺፋና አቶ ገብረ ማርያም እንደተገናኙ ለክፋት አልተፈላለጉም። ይልቁንስ አዝማቹና አቶ ገብረ ማርያም በፍቅር ተቀራረቡ። አልፎም ተርፎ እኒያው አሳዳጅ አዝማች ለባላንጣቸው በጎ ተመኙላቸው። «አንተ የምታምነውን የመሰለ ክርስትና የሚከተሉ ሌሎችም ሰዎች እዚሁ በቅርብ አሉና ባገናኝህስ?» ብለው ይጠይቋቸዋል። የኦርቶዶክስ እምነት አጥባቂው ዲያቆን ገብረ ማርያም የተመከሩትን ለመፈጸም አላንገራገሩም።

ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፊት ለፊት (በቀድሞ ስሙ ራስ ተሰማ ሠፈር) ገና በመቆርቆር ላይ ወደ ነበረው የሱዳን ኢንቴርዩር ሚሲዮን ግቢ አቶ ገብረ ማርያምን በመውሰድ ከሚሲዮናዊያኑ ጋር አስተዋወቋቸው። ለአቶ ገብረ ማርያም ክርስቲያን ይሁን እንጅ የፈለገ ሰው የወንጌልን እውነት ቢያስተምራቸው ግድ አልነበራቸውም። እንደተመኙትም የተጠሙትን ወንጌል እየተማሩ መርካት ጀመሩ። ጌታ ኢየሱስንም እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በ1941 ዓ.ም ተቀበሉ። እዚያው በሚሲዮኑ ግቢ ውስጥም የአናጢነት ሥራ እንዲሰሩም መንገድ ተከፈተላቸው። ከተወሰኑ ቀናት በኋላም መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ወደ አካባቢያቸው ተመለሱ። የአካባቢው ሕዝብ ግን አዲሱን እምነታቸውን አልወደደላቸውም። ቤተ ዘመድ አብዱል፥ የአካባቢው ካህናት ደግሞ ገብረ ማርያም በቁሙ ሞቷል በማለት ማስወራት ጀመሩ። ፅኑው ገብረ ማርያም ግን አልተበገሩም። ሌሎች የወንጌል ሰዎች ይገኛሉ የተባሉበትን ቦታ ማፈላለጉን ተያያዙት። ይህን መሻታቸውን የተረዱ ሰዎች እዚያው በቅርባቸው በሃዲያ ክልል ውስጥ አንጋፋው የወንጌል ሰው አባ ጎሌ ኑነሞ መኖራቸውን ይገልጹላቸዋል። ጊዜ አልሰጡም። በተነገራቸው ምልክት መሠረት አባ ጎሌ ኑነሞን ለመገናኘት እንደገና ወደ ሃዲያ ምድር ያቀናሉ። ድካማቸው ከንቱ ሆኖ አልቀረም። አባ ጎሌን ተገናኝተው ወደ አካባቢያቸው ተመለሱ። ተመልሰውም አላረፉም። ለመጀመሪያው የአምልኮ ጣቢያነት የራሳቸውን ጎጆ ሰጡ። አዘገጃጁ። ጊዜው እየገፋ ሲሄድ የዚንዚቾው የኤስ.ኤይ.ኤም ሚሲዮን ጣቢያ ተከፍቶ ድጋፍ ሆናቸው። ድጋፉቸው ብዙም አልሰነበተም። ለውጡ እንደመጣ የሚሲዮን

ጣቢያው ወዲያው ተዘጋ። የሚሲዮን ጣቢያው መሥራችና አዲስ ኪዳንን ወደ ጉራጊኛ ያስተረጎሙት ሚ/ር ሐዊ ብራንትና ቤተሰቦቻቸው አካባቢውን ለቀው ወጡ።

ያም ቢሆን ግን አንድ ነፍሳቸውን ሆነው የጀመሩት የቤተ ክርስቲያን መሠረት አራት መቶ ያህል ምዕመናን አፍርቶ አምልኮው በስምንት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እየተካሄደ ነበር። የጉመርን ምድር ለወንጌል ማሳነት የተጠቀመበት አቶ ገ/ማርያም ጭሞቼ ጊዜው ሲደርስ በ1972 ዓ.ም. በመከራ ውስጥ እንዲያልፉ ግድ ሆነ። መስከረም 18 ቀን 1972 ዓ.ም የታጠቁ የአካባቢው የጸጥታ ኃይላት ድንገት በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ወረራ በመፈጸም ቤታቸውን፥ በደጃፋቸው ላይ የተመ ሰረተችውን ቤተ ክርስቲያንና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት እንዳለ ዘረፉ። በተለይም ወንጌላዊያን ይጠቀሙባቸው የነበሩትን 13 ያህል በሰው ኃይል የሚዘወሩ ቴፖችንና ሌሎች ንብረቶችን በግዳጅ አግበስብሰው ወሰዱ። የተቀረውን ንብረት አጓጉዘው እስኪጨርሱ ድረስም የፈለጉትን አሽገው ሄዱ። አቶ ገብረ ማርያምንም ወደ ወጎኒ ቤት መረመሯቸው።



አቶ ገብረ ማርያም ጭሞቼ

አቶ ገብረ ማርያም ግን ያንን ግፍ የተሞላበት ትዕይንት እየተመ ለከቱ ማለፍ አልቻሉም። ውስጣ ቸው እየደበነና እያረረ ነጋ ጠባ በወህኒ ቤት ውስጥ እንዳሉ ባሎላካ ችው ፊት ግልቀሱን ተያያዙት። ልጃቸው አቶ ፍቅሬ ገብረማር ያም እንደገለጹልን ከሆነ ህመም የግያውቁት ገብረ ማርያም ታማሚ መሆን የጀምሩት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። የውስጣቸው የህ ሊና ቁስልና ህመሙ ስለጸናባቸው እር ሳቸውን አስሮ ከማስተማም ለጊዜ ውም ቢሆን እስኪሻላቸው ድረስ ሆስፒታል ይቆዩና ሲሻላቸው ወደ ወህኒ ቤት ይመለሱ የሚል «ፍታድ» ተሰጣቸው። እናም ሆስፒታል ገቡ። ተሽሏቸው ወደ ወህኒያቸው ከመመለሳቸው በፊት ግን በዚያው በሆስፒታል ውስጥ አርፈው ወደ አምላካቸው እቅፍ በመሰብሰባቸው አገልግሎታቸውን ፈጸሙ። ባለቤታቸው እማማ ወ/ሚካኤል በባለቤታቸው ሞት አልተረቱም፤ ቤታቸውን ይብልጥ ለመስተንግዶና ለአገልግሎት በመክፈት የወንጌሉ ሥራ እንዲሮጥ አመሩ።



አቶ ገብረ ማርያም ጭምቹ

የአቶ ገብረ ማርያምን ሞት አስከትሎም በአንድ ቀን ትዕዛዝ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ተዘጉ። ብዙ ክርስቲያኖችም እየተለቀሙ ታሠሩ። የጉራጌ አማኞች ይህን መሰሉን ግፍ እያዩ ሊታገሱ አልቻሉም። እስራት የማይቀርልን ከሆነ አንድ ቀንም ቢሆን በተዘጋው የጸሎት ቤታችን ውስጥ አምልከን ለዘለዓለም እንታሰር ብለው በመወሰን ጨከኑ። ሞካኔያቸውና ምሬታቸው ወደ አንድ ውሳኔ አደረሳቸው። የተዘጉትን ቤተ ክርስቲያናት በኃይል ከፍቶ በመግባት ዝማሬውንና አምልኮውን ለማቅለጥ ተስማሙ። ተስማምተውም ፈጸሙት። እውነትም እምነት ደጉ በኃይላቸው የከፈቷቸው የጸሎት ቤቶች ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ልዩ ጥበቃ እንዳሉ ናቸው። የነበሩት እንደነበሩ ሆነው ሌሎችም አጥቢያዎች ተወልደዋል። አቶ ገ/ማርያም ሞሞቼ አንድ ብቻቸውን ሆነው በቆሙበት ምድር ላይ ዛሬ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ምዕመናን የወንጌሉን አዝመራ እያዘመሩ ይገኛሉ።[175] በጉመር ምድር ላይ የወንጌሉ አዝመራ እንዲዘምር አቶ ገብረ ማርያምን በመደገፍና በርካታ ወንጌላዊያንን ያሰማሯቸው የሃይያ ማኅበር ዛሬም ድረስ የምትታወሰው በታላቅ ፍቅርና ክብር ነው ፤ የተዘራው የወንጌል ዘር አልመከነምና።

እንግዲህ ምን እላለሁ?

ማረቆ

በ1944 ዓ.ም አቶ ፋንታ ኑኖ የተባሉ አዛውንት ከከንባታና ሃዲያ ወደ ማረቆ ያመራሉ። እዚያም እንደደረሱ ቀድመው ላገኟቸው ለአቶ ሜቼ ጡምደዶ እና ለአቶ ሶሰምሮ ጡምደዶ የምሥራቹን ቃል ይነግሯቸዋል። ማረቆዎቹ ሜቼ እና ሶምሮ ለሰሙት ቃል አሜን አሉ። የወንጌሉ ብርሃን በልባቸው ውስጥ የበራላቸው ሁለት ሰዎች በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው እየበረከተ ሄደ። መበርከት ብቻ አይደለም፤ ሆቤ በተባለው ሥፍራ የራሳቸውን አጥቢያ መሠረቱ። ይህን የቅዱሳን ስፋት ያስተዋሉ ሌሎች አርፈው አልተኙም። ማረቆዎችን በስደት አጣደፍዋቸው። ብዙዎቹንም እያሠሩና እየገረፉ አስጨነቋቸው። በአስጨነቋቸው መጠን ግን የማረቆ ክርስቲያኖች ቁጥር እጥፍ ጊዜ እጥፍ እየበዛ ሄዶ ሰላሳኛውን ዓመታቸውን ለማክበር በሚያስችላቸው የ1974 ዓ.ም ላይ ደረሱ። ያኔ ምዕመኑ ወደ 210 ሲደርስ አጥቢያዎችም ወደ አምስት ደርሰው ነበር።

---

175 የታሰ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ ያልታተመ፤ 1978 ዓ.ም. ፤ የአቶ ገብረ ማርያም ልጆች የአቶ ደገፉ ገብረ ማርያም የጽሑፍ ማስታወሻና የአቶ ፍትሬ ገብረማርያም የታሰ መግለጫ፣ መጋቢት 14 1992 ዓ.ም.

በዚህ ወቅት ነበር ከማረቆዎች ተለይቶ የማያውቀው ስደት በአዲስ መልኩ እንደገና ያቆጠቆጠው። የለመዱት የስደት በትር ክፉኛ አረፈባቸው። አጥቢያዎች በሙሉ ተዘጉ። ብዙ ምዕመናንም ታሠሩ። አልፎም ተርፎ በአምልኮ አብረው ሲተባበሯቸው የኖሩት በጊዜው የክህደት ነፋስ ተወስደው የጭቃ ውስጥ እሾህ ቢሆኑባቸውም ማረቆዎች ግን እጅ አልሠጡም። አሻግረው በሚያዩት ተስፋቸው እንደጸኑ ጋላፊውን ዘመን አሳልፈዋል። ዛሬ የማረቆ አጥቢያዎች በርከተዋል፤ የምዕመኑም ቁጥር የዚያንው ያህል በርክቷል።

አርሲ

በመጨረሻ ወደ መጀመሪያው በረከት

ወንጌል ወደ አርሲ *(ቀደም ሲል አሩሲ በሚባለው ስም ይታወቃል)* እንደገባ የሚታመነው በ1937 ዓ.ም. ነው። ሲራር የምሥራቹን ቃል ይዘው የመጡትን እንግዶች ተቀብላ የሮጲ ቀበሌ ማረፊያቸው ሆነ። በወቅቱ የአርሲ አብዛኛው ክፍል በደንና በጥሻ የተሸፈነ ስለነበር ገላጣ ሜዳ ማግኘት ብርቅ ነበር። ሰንበሌጡ ከሰው ቁመት በላይ ስለነበር ሰውና የዱር አራዊቱ እየተጋፉ ነበር የሚኖረው። አካባቢው እንዲህ የተፈጥሮ ድንግል ይሰኝ እንጂ የሰውም ልብ የዚያንው ያህል ድንግል ነበር ለማለት ይቻላል። አብዛኞቹ አርሲዎች በወቅቱ ይህ ነው የሚባል እምነት ስላልነበራቸው አምልኮአቸውን ይፈፅሙ የነበረው በወንዝ፥ በተራራ ወይንም በሰማይ ሠራዊት እና በመላሰሉት ግዑዛን ፍጥረታት እንደነበር ዛሬ በክርስትና እምነት ውስጥ ያሉት አባቶች ይመሰክራሉ። አብዛኛው ሕዝብ ከብት አርቢ ስለነበር ጦሩን በትከሻው ላይ አድርጎ፥ ጎራዴውን በወገቡ ላይ ሸጦ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስ ነበር።

በዚህን ወቅት ነበር ኤልሻዳይ ለአርሲዎች ወንጌል እንዲሰበክ የመልዕክተኞችን ልብ ማዘጋጀት የጀመረው። የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚዎቹን መልዕክተኞች በመላክ ለአርሲዎች ባለውለተኛ ስትሆን፤ ለአምላኳም ታዛዥ ሆናለች። ወንጌላዊ ጋሎሬ ገረደ፥ አቶ በዛ ባካሎ፥ አቶ ሐደራ ሐንቱኬ፥ አቶ መና አካኮ፥ አቶ ሹንቄ ሻለም፥ አቶ ጋኔቦ ጋጋ እና ሌሎችም በቀዳሚ የወንጌል መልዕክተኝነት የሚጠቀሱ ባለታሪኮች ናቸው። ወንጌላዊያን ወደ አርሲ የገቡበት ዓመታት የተለያዩ ቢሆኑም ሁሉም እና በዚህ ገጽ ላይ ዝርዝርዝዝቸው ያልተጠቀሱት ሌሎችም በመተባበር በድንግሉ የአርሲ ሕዝብ ልብ ውስጥ የወንጌሉን ዘር ያለመታከት መዝራት ጀመሩ።

አርሲዎች ከብቶቻቸውን ይዘው ከሥፍራ ሥፍራ ሲንቀሳቀሱ ወንጌላ ዊያኑም ሳይደክሙ እየተከተሏቸው ባረፉበት እያረፉ፥ በዋሉበት እየዋሉ የምሥራቹን አወሩላቸው።

በታሪክ መዘክርነቱ መታወሱ አግባብ ስለሆነ የወንጌላዊያኑን ወደ አርሲ አላላክ ስልት በተመለከተ የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ትጠቀምበት የነበረውን ዘዴና በ1940ዎቹ ጎደማ መልዕክተኞቹ እንዴት ራሳቸውን በፈቃደኝነት ለወንጌል አገልግሎት ይሠጡ እንደነበር በ1989 ዓ.ም በ96 ዓመታቸው ያወጉንን የአቶ ሐደሮ ሐንቱኬን የምሥክርነት ቃል እናስነብባለን፤

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አወደው የነበረው ከልጅነቴ ጀምሮ ነው። ብዙ የቀለም ትምህርት ባይኖረኝም መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ያህል ግን ዕውቀት አላጣሁም። አንድ ቀን ድጉና በሚባለው የእኛ ማኅበር ውስጥ ትልቅ ኮንፍራንስ ተዘጋጅቶ ነበር። በዚያ የወንጌል ኮንፍራንስ ላይ ለእግዚአብሔር ሥራ ራሱን የሚሰጥ ሰው በዚህ ጉባዔ ውስጥ ካለ ተብሎ ተጠየቀ። እኔ ተሽቀዳድሜ ተነሳሁ። አልዘገየሁም በሲራሮ ወረዳ ወደ ሮጲ ቀበሌ ለወንጌል ሥራ ወዲያው ተላክሁ። በዚያን ወቅት እንደተመቻቸው በሦስት ወርም ከዚያም በላይ ብር 10 ያህል ማህበሬ ሰንቅ ይልክልኝ ነበር።[176]


የአቶ በዛ ባካሎ ምሥክርነትም ተመሳሳይ ነው። አቶ በዛ ለወንጌል ሥራ ወደ አርሲ በተላኩበት ወቅት የወላይታ የጠረጴዛ ሽግግሌዎች *(የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ)* ይከፍሏቸው የነበረው አስር ሣንቲም ነበር። ያቺንው ጥቂት ሣንቲም አጠረቃቅመው የልብስ መስፊያ መርፌ፥ መርፌ ቁልፍና ጥቃቅን እቃዎች ይገዙ እንደነበር በአንደበታቸው የተረኩት ታሪክ ያስረዳል።

እነዚህ የወንጌል አርበኞች በአርሲ ውስጥ በሚያገለግሉበት ዘመን ብዙ አስገራሚ ታሪኮችን እንዳሳለፉ አቶ አኖታ ጋንጌሶን የመሳሰሉ አንጋፋ የህገሬው አማኞች የሚመሰክሩት ብዙ ነው። ከብዙው አንዱን አቶ አኖታ እንደሚከተለው ተርከዋል፤

ዘመኑን በሚገባ አላስታውስም። ብቻ በአንድ ወቅት በሮጲ ቀበሌ ውስጥ አማኞች ተሰብስበን እያመለክን እያለ ድንገት በፖሊስ ተከበብን። የፖሊሶቹ ኃላፊም እናንተ ምንድን ናችሁ? ብሎ ጠየቀን። እኛም ማኅበር ያለን

[176] አቶ ሐደሮ ሐንቱኬ፤ ቃለ መጠይቅ፤ 1989 ዓ.ም.

አማኞች ነን ብለን መለስንለት። እርሱም አለቃችሁ ማነው? በአስቸኳይ ንገሩን አለን። እኛም አለቃችን ኢየሱስ ነው ብለን መለስንለት። ፖሊሱም በጣም ተናዶ በአስቸኳይ ይሄ ኢየሱስ የተባለው አለቃችሁ መጥቶ እንዲታሰር ብሎ ወሰነ። እኛም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሊታሠር አይችልም ስንለው በቁጣ ተበሳጭቶ ለግምት 25 የምንሆን ሰዎችን ወደ ሻሸመኔ በመውሰድ አሳሰረን።[177]



የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባቶች
ከግራ ወደቀኝ አቶ ባቲ ኻርሶ፣ አቶ በዛ ባካሎ፣ አቶ ሙና ጡኒና አቶ ሐሶ ዋጪ

የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና ዕድገት ይህን የመሰሉ አስደናቂ ታሪኮች የተስተናገዱበት ቢሆንም ከሰላሳ ዓመ ታት በኋላ ምዕመናን ይታሠሩበት የነበረው የሻሸመኔ እስር ቤት እንደገና ለሌላና አዲስ መስተንግዶ ታጨ። በወቅቱ እየሰፋችና እያደገች የነበረችው የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ራሷን ሻሸመኔ ክፍል፣ ወንዶ ክፍል፣ ወተራ ክፍል፣ ነጌሌ አርሲ ክፍል በማለት ከ37 በላይ በሆኑ አጥቢያዎች ወንጌሉን ለማብሰር ስትጣደፍ በክህደት የተሞላው የኮሚዩኒዝም ሥርዓት በምእመናን ላይ ጊዜያዊ ጫና ሠነዘረባቸው። ሠንዝሮ ብቻ አልተወም በርካታዎቹ አጥቢያዎች እንዲዘጉ ተወሰነ። ምዕመናንም ለእስርና ለስቃይ ተዳረጉ። ለጊዜው የታቀደው የግፍ ጽዋ

---

[177] አቶ አኖታ ጋኔሶ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 1989 ዓ.ም.



የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባቶች
ከግራ ወደቀኝ አቶ ባቲ ጃርሶ፥ አቶ በዛ ባካሎ፥ አቶ ሙና ጡኒና አቶ ሐሶ ዋጪፎ

የሞላ ይምሰል እንጂ በእግዚአብሔር አምላካችን ቀን ጽዋው ሲገላበጥ ታሪኩም እንዲሁ የተገላቢጦሽ ሆኖ የእግዚአብሔር ሕዝብ በነፃነት ሊያመልክ ጊዜው ደረሰ። የተዘጉት ተከፈቱ። የታሠሩት ተፈቱ። በርካታ አጥቢያዎችም እየተተከሉ ወንጌል በመስፋፋት ላይ በነበረበት የሥራ ወቅት ሌላ አዲስ አበሳ በአርሲ ምእመናን ላይ መፈጸም ተጀመረ። በ1983 ዓ.ም. በአርሲ ምድር የተለየ ወቅት ወለድ የነጣ ችግር ፈንድቶ ወጣ። በዚሁ ምክንያትም ከአርሲ ከልል ውጭ የመጡ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ከአካባቢው ተባረሩ። ከስድስት በላይ የሆኑ ከሳር ክዳን የተሰሩ የጸሎት ቤቶች ተቃጠሉ። ከቆርቆሮ የተሠሩ አጥቢያዎችም እየፈራረሱ ተዘረፉ። የአርሲ አማኞችና መከራ የተቀራኙ ስለሆኑ ችግሩ አጠከራቸው እንጂ ጉልበታቸውን አላላላውም። የክርስቶስ የፍቅር ወንጌል በመለያየት መካከል ተሰበከ። የተፈናቀሉት ክርስቲያኖች በችግራቸው ውስጥ የክርስቶስን የተለየ ፍቅርና በወንጌሉ የተገኘውን የሰላም አዋጅ ለማብሰር አጋጣሚው መልካም ሆነላቸው። ዛሬ የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ተረጋግተው እያመለኩ ይገኛሉ። በመከራውና በችግሩ ውስጥ የበዙትን ቅዱሳን ጎብረት ጠብቆ የምሥራቹን ለማወጅ የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በጽናት እየሠራች ነው።[178]

"... ነገር ግን እንዳስጨነቋቸው መጠን እንዲሁ በዙ፥ እጅግም ጸኑ።"
(ዘፀአት 1፥12)

ጅማ

"በተሰፋ ቃል በተሰጠው ሀገር... በእምነት ተቀመጠ።" (ዕብ. 11፥9)

በዶ/ር ላምቤ የተመራው የመጀመርያው የኤስ.ኤይ.ኤም ሚሲዮናዊያን ቡድን መድረሻውን ለማድረግ ያሰበው ጅማ ቢሆንም የእግዚአብሔር አምላክ ፈቃድና አጀንዳ ግን የተለየ ነበር። ጅማ እስክ ዕለተ ቀኑ ድረስ በትዕግሥት ጠበቀች። እናም የደህንነት ወንጌል በተመሰ ነላት ዕለት የከፋን አካባቢዎች ማንኳኳት ጀመረ። በ1930ዎቹ ዓመታት ገደማም በኤስ.ኤይ.ኤም ሚሲዮን ጣቢያዎች አካባቢ መሰበክ የተጀመረው ወንጌል እየሰፋና እየበዛ ምድሪቱን ለማዳረስ በፍጥነት መሮጥ ጀመረ።

---

[178] የአርሲ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያልታተመ፣ 1978 ዓ.ም. እና የቃለ ሕይወት ቤ/ክርስቲያን ታሪክ ያልታተመ ገጽ 100 ፤1978 ዓ.ም.

ይህንን የወንጌል ሩጫ ለመግታት ነው በ1970 ዓ.ም. መቀጣጠል የጀመረው ስደት ሙከራ ያደረገው። ቀደም ባሉት ክፍሎች ለማወልከት እንደተሞከረው የጂግው ስደት ተባባሪዎች በመቶዎችና በሺህዎች የሚቆጠሩ ነበሩ። እነዚህ የአድማ ተባባሪዎች ሆ! ብለው በሰላማዊ ሰልፍ በመዝመት የአካባቢውን የጸሎት ቤቶችና የጅማን የምልዓተ ጸጋ መጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚን ሙሉ ለሙሉ የዘረፉትና ያወደሙት በመጋቢት ወር 1970 ዓ.ም. ነው። የጂግና አካባቢው የታለ ሕይወት ቤተ ክርስ ቲያናት ስደት ከሌሎች አካባቢዎች ይልቅ ላቅ ያለና የመረረ ስለነበር እንዳንዱን ታሪክ ብቻ ጠቅሶ ማለፉ አግባብ ይሆናል።

መጋቢት 20/1970 ዓ.ም. ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ የአካባቢውን ከፍተኛ ሹማምንት፥ መታደርችንና የፖሊስ አባላትን የሜን ሦስት የላንድሮቨር መኪናች ወደ ምልዓተ ጸጋ የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ እየበረሩ በመጣት በግቢው ውስጥ ቆሙ። በመኪኖቹ ውስጥ የነበሩት ፖሊሶችና መታደርች ከመቅጽበት በግቢው የተለያዩ በታዎች ደፈጣ በግድረግ ምድረ ግቢውን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ።

ከአንድ ሰዓት በኋላም ቁጥራቸው 3000 የሚገመት መጣቶችና ነዋሪዎች በሰልፍ እየተመሙ ወደ ግቢው ውስጥ በመግባት በመፈክር፥ በርግግንና በጩኸት ሰላማዊውን አየር አናወጡት። ከዚያ በኋላማ ምኑ ይነገራል ያ አንደንብ ሠራዊት እየተመመ የመጣውን ሕዝብ ምንም የሚገታው ኃይል ስላልነበረ የፈለገውን ፈጸመ፥ የዘረፈውን ዘረፈ፥ ያወደመውን አወደመ።

በግግሥቱም እንደተለመደው በአራት መኪኖች ከፍተኛ የመንግሥት ሹማምንቶች በተለመደው አኳኋን ግቢው ድረስ በመምጣት የአካዳሚውን የሥራ መሪዎች፥ ሠራተኞችና ተማሪዎችን በሜዳ ላይ በመሰብሰብ በአብራት የተሞላ ዝምና ውሳኔ ሰጡ።

የአመጹ አስተባባሪ የነበሩት የፖሊስ ኮሎኔል ድምፃቸውን ዘለግ አድርገው የሚከተለውን ውሳኔ አስደመጡ። በግቢው ውስጥ የነበሩት የአካዳሚው ዳሬክተር ሚ/ር ፖል ብልስኪ፥ ባለቤታቸው ሚስስ ላይላ ብልስኪ፥ ሦስት ህፃናት ልጆቻቸውና ሚ/ር ብርያን ፋርገር የከፉ ከፍል ሀገርን በ24 ሰዓት ውስጥ ለቀው እንዲወጡ መወሰኑ ተገለጸላቸው። ይህም እንቅስቃሴ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ እንዲከናወን ኮሎኔሉ አበክረው አሳሰቡ። ሌላው ጥብቅ ትዕዛዝ ደግሞ ሚስዮናዊያኑ ከለበሱት ልብስና ከሌሊት ፒጃማቸው በስተቀር አንዳችም ፅታ በእጃቸው ይዘው እንዳይወጡ መታገዳቸው ነው። በመሆኑም የየቤቶቻቸውንና የመኪና

ቁልፎችን እንዲያስረክቡ የተደረገው እዚያው በቆሙበት ቦታ ላይ ነበር። ከዚህ በኋላ እንደታዘዙት ሚሲዮናዊያኑና ህፃናት ልጆቻቸው ወዲያው በአውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተላኩ።

ሚሲዮናዊያኑ ከተባረሩ በኋላ የአካዳሚው ም/አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ግርማ ሀናኖ በቁም እስረኝነት ለ35 ቀናት ያህል በግቢው ውስጥ በየፅለቱ እየተመረመሩ ከቆዩ በኋላ እንደሚሲዮናዊያኑ ሁሉ ምንም የግላቸውን ንብረት ሳይዙ ከአካዳሚው እንዲለቁ ተወሰነ። ተማሪዎችም እንዲሁ ለጥቂት ቀናት ያህል እዚያው ከሰነባበቱ በኋላ ወደየመጡበት አካባቢ ተበታተኑ። በግፈኞች እጅ የወደቀው የምልዓተ ጸጋ የመጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ ዕጣ ፈንታ ከዚያ በኋላ ምን ሊሆን እንደሚችል አንባቢው መገመት ይችላል።[179]



በ24 ሰዓት ውስጥ ጅማን ለቀው እንዲወጡ የታዘዙት ዶ/ር ፖል ብልስቢና ቤተሰባቸው

በመጋቢት ወር 1970 ዓ.ም. የገነፈለው የጂማው ስደት ተፋፍሞ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን መግቢያና መውጫ እስኪያጡ ደስ በአሳዳጆቻቸው እየተዋከቡ ዓመቱን እንዲሁ በእንባ አሳለፉት።

መከራው የመከበዱን ያህል ምዕመኑም እንዲሁ በእምነታቸው እየጸኑ ሄዱ። በ1971 ዓ.ም. የጂማ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

---

[179] Report, brief account of details of last week at SIM, Jimma, March 23 -31, 1978.



በ24 ሰዓት ውስጥ ጅማን ለቀው እንዲወጡ የታዘዙት ዶ/ር ፖል ብልስኪና ቤተሰባ

የመዘምራን ቡድን በአቶ እስራኤል ገብረየስ ቤት የዘመኑን የገና በዓል በጎብረት አከብሮ ለመዋል ይወስናል። በዚሁ መሠረትም እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የከሰዓት በፊቱን ፕሮግራም በዚያ ቤት አጠናቀው ለከሰዓት በኋላው ቀሪ ፕሮግራም ደግሞ የግድ ቦታ መለወጥ ስለነበረባቸው የመዘምራን ቡድኑ አባላት ዱካቸውን እያጠፉ ቀስ በቀስ ተደብቀው አንድ በአንድ እየወጡ በአትራቢያ ወደሚገኘው ወደ አቶ ገብረ ሥላሴ ዱከም ቤት ተሰባሰቡ።



የምልዓተ ጸጋ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የ1969 ዓ.ም. ተግሪዎችና ምሩቃን





የመጨረሻዎቹ ተግሪዎች . . .



የምልዓተ ጸጋ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የ1969 ዓ.ም. ተማሪዎችና ምሩቃን





የመጨረሻዎቹ ተማሪዎች . . .

ለካንስ በዚህን መሃል በምሥጢር ይከታተሏቸው የነበሩ የፖለቲካ ሰዎች ስለነበሩ እነርሱ ባደረጉት ፈጣን ጥቆማ መሠረት የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ የነበሩት ሻምበል ተሰማ በላይ የክፍለ ሀገሩን የፖሊስ አዛዥ ኮሎኔል ተድላን አስከትለው በመምጣት የመዘምራን ቡድኑ አባላት የነበሩበትን ቤት ይከባሉ። በመቀጠልም እያንዳንዱ የመዘምራን ቡድን ሰልፍ ከያዘ በኋላ ርጎራሄ በጎደለው ሁኔታ ኢሰብዓዊ ቅጣት ተፈጸመባቸው። እንደ ከፍተኛ ወንጀለኞች ተቆጥረውም በአምቡላንስ መሰል አደጋ ጠቋሚ መኪና እየተመሩ ወደ ልዩ መቀጣጫ ሥፍራ ተወስደው ሌላ ዙር ቅጣት ተቀበሉ። ከወጣቶቹ መካከል ጎላ ብሎ ይታይ የነበረው አቶ አስፋው ደፋርም እንደ ዋነኛ የአሜሪካ የስለላ ድርጅት (ሲ.አይ.ኤ) አባል ተቆጥሮ በተለየ አካላዊና ጎሊናዊ ቅጣት ተቀጣ።

የዚያን ዕለት ምሽትም የከተማው ወጣት በሙሉ ተሰብስቦ የሞት ቅጣት እንዲፈረድባቸው ተደረገ። ውሳኔው ተግባራዊ ከመሆኑ አስቀድሞ ግን ከአዲስ አበባ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስትያን ማዕከላዊ ማስተባበሪያ ቢሮ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በአስቸኳይ ሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር ድረስ በመሄድ አቤቱታ ስላቀረበ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ የሞት ፍርዳቸው ሊዘገይ ችሏል።

መከራውና ስደቱ ከጂማም አልፍ ብሎ ወደ ሚዛን ተፈሪ አውራጃ በመዝለቅ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና በሌሎችም ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ላይ ተፋፋመ። በሙሉ ክርስቲያኖች ታድነው እንዲያዙ ከተደረገ በኋላ በልዩ የማሰቃያ ክፍል ውስጥ ሰውነታቸው እየተዘቀዘቀ ቶርች በሚባለው የቅጣት ዓይነት የውስጥ እግራቸውና ገላቸው እስኪሞሸለቅ ድረስ በጉማሬ በየዕለቱ ይገረፉ ነበር። በማሥቱም ቁስላቸው እንዳያመረቅዝና ደም እንዳይቋጥር በአሸዋ ላይ እንዲዘሉና በጠጠር ላይ እንዲንከባለሉ ይደረግ ነበር። ከዚህም አልፎ ተርፎ ሙሉውን ሌሊት ታስረው ያድሩ ስለነበር እጃቸው ሽባ እንዳይሆን በየዕለቱ ጠዋት ጠዋት ስፖርት የመሥራት ግዴታም ነበረባቸው። የእስረኞቹ ዋና ወንጀል «ለምን ጴንጤ ሆናችሁ? ማነው እየመለመለ ወደ ጸሎት ቤት የሚያስገባችሁ? ወ.ዘ.ተ.» የሚል ዓይነት ነበር። ምላሽ እንዲሰጡባቸውም በርካታ ጥያቄዎች ይሰነዘርላቸው ነበር። ለአብነት ያህልም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በሀገር አቀፍ ደረጃ፥ በአውራጃና በቀበሌ እንዴት ነው የተዋቀረችው? በየደረጃው ያሉ መሪዎችስ እነማን ናቸው? የሚሉ ዓይነት ጥያቄዎች ነበሩ። እስረኞቹ «ምላሹን እኛ አናውቅም። ቃለ ሕይወት ሕጋዊ ድጋፍ ያላት ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች በራሳችሁ መንገድ ማጣራት ትችላላችሁ» እያሉ

በመመለሳቸውም የበለጠ ስቃዩ ሊጀረታባቸው ችሏል። ከስቃዩ ነገ ለነገም በእምነታቸው ምክንያት የታሰሩት መንደሩ እስረኞች ለመሆኒ ቤቱ ሌሎች እስረኞች የመፀዳጃ ቤት ጉድጓዶችን እንዲቆፍሩና ለምግብ ማብሰያ የሚሆን እንጨት እንዲለቃጡ ተመለኑ። ሴት አማኞች ደግሞ ለእስረኞቹ በሙሉ እንጀራ እንዲጋግሩና ወተ እንዲሰሩ ተመለካቸው። ያም ቢሆን ግን ክርስቲያናቹ ለመከራውና ለሥራ ትጥቱ ያለመበገራቸውን ያዩት ሹሞች ሌላ ዘዴ በመተየስ እስረኞቹ እንደሚፈቱ ማስታወቅ ጀመሩ። ግንም ክርስቲያን ተፈትቶ ወደ ሰላማዊ ናር ለመተላለፉ ከፈለገ መጽሐፍ ቅዱስን በሕዝብ ፊት እንዲያቃጥልና መስተል ረግሙ እንዲራመድ ምርጫ ተረበላቸው። ጽኑእኑ የክርስቶስ አርበኞች ግን በጊዜያዊ መከራና ከሀዲት ሳይናወጡ የአምላካቸውን የፍርድ ፈለት በተስፋና በጽናት በመጠበቅ በመለማምቹ የከሀዲት ዓመታት ለማለፍ ጥርሳቸውን ነከሰው በረቱ። የእምነታቸውንም ብርታት አጸኑ። አምላካቸውም ከሰማይ ተመለከታቸው። የእስራታቸው ሰንሰለት የሚፈታበት ወቅት ደረሰ። የተሰፋ ትህኖ ፈነጠቀ።

መከራው የመፖረሩና የሌሊቱ የጭ ጨኽት የመብዛቱን ያህል ሃሴትና የሃሌሉያው ዝማሬም የዚያንው ያህል በእዝያ የመከራ ዓመታት የከፋን ምድር አጥለቅልቆ ነበር። የመከራው ዘመን ሲያበቃና የስደቱ ቀንበር ሲፈታ እንደገና ቅዱሳን ለአዲስ የወንጌል ሥራ ተነቃቁ። በጅግ ምድር ሃሌሉያው ቢገንን እውነት ኩለው። በሥር ተጨቅጭቆ የሞተው የወንጌላዊ ተሰማ ዱቢ ደምና የእዝያ ምዕመናን እንባና ጸሎት ብዙ ፍሬ አፍርቷልና።

እንግዲህ ምን አላለሁ? . . .

ስለ አዋሳና ስለ ቁጫ

ስለ ደሌና ቦሩ ሜዳ

ስለ ዲባጤ

ስለ ደብረብርሃን

ስለ ሌሎችም እንዳልተርከ የመጽሐፉ የገጽ ውሱንነት ተፈታተነኝ። ወንጌሉ የርጠባቸው እነዚህ አካባቢዎችና ሌሎቹም የደመቀ የራሳቸው ታሪክ አላቸው። ስግቸውንና አድራሻቸውን ለመጥቀስ የግንችላቸው ብዙ ቅዱሳን ያንን የስደት ኤሎሄ በሃሌሉያ ዝማሬ አልፈውታል። እየዘመሩ ብቻ ሳይሆን ነፍሳትን ለአምላካቸው እየማረኩም ጭምር መከራውን ተሻግረውታል። የዛሬዋ የታለ ሕይወት

ቤተ ክርስቲያን መልክ የወጣውና የፈካው እነዚያ ቅዱሳን ልጆቿ በመከራ ውስጥ ነጥረው ባገኙት የጸጋ ትጥቅ ነው። እንግዲህ ምን እላለሁ? . . . የአዋሳ፥ የደሴ፥ የቋሜ፥ የሳቻ፥ የቦሩ ሜዳ፥ የዲባጤ፥ የደብረ ብርሃንና ሌሎችም ስማቸውን ያልገለጽናቸው የብዙዎች ታሪክ የዕብራዊያን መጽሐፍ ጽሐፊ ከጠቀሳችው ታሪኮች ጋር የሚመሳሰሉ በርካታ ታሪኮች አሏቸው፤

ጻንርሉ በእምነት ደል ኑ። . . . ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፥ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በሠርንት ኃይለኞች ሆኑ . . .
የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ምት ድረስ ተደበደቡ፤
ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ
በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤ . . . ሁሉን እያጡ መከራን
እየተቀበሉ፥ እየተጨነቁ . . . ተትበከበሙ።»
(ዕብራውያን 11፡32–40)

የምዕመኗ ቁጥር በአራት ሚሊዮን የአጥቢያዎቿም ብዛት በአራት ሺህ ሊቆጠር የበቃው የታለ ሕይወት ቤተ ክርስትያን ውበት ሊደምቅ የቻለው በእነዚህ መሰል የመከራ ጎብር ስለተሸረበ ነው። ታሪኳ ታሪክ ሊሆን የበቃውም የልጆቿ የመከራ ውጪትና የአምላኳ ልዩ ርዳታ ስለታከለበት ብቻ ነው። ለብርታቷና ለብቃቷ ጉልበት የሆናት የአምላኳ የምህረትና የቸርነት እጆች ብቻ ናቸው። መአዛዋ ገንኖ ሊወጣ የቻለው ልጆቿ የከፈሉት የምድራዊ የመስዋዕትነት ውጪት እንደ ሻማ ስለሚያበራ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷ ጀግሬና ፈጻሚዎ አምላኳ ብቻ እንደሆነ ታረጋግጣለች። ይሄው ነው።

እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን
ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ፥ ቶሎም የሚከብደንን
ኃጢአት አስወግደን የእምነታችንንም ፊሰና ፈጻሚውን
ኢየሱስን ተመልከተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት
እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ
በመስቀል ታገሰ በእግዚአብሔር
ዙፋን ቀኝ ተቀምጧልና።
(ዕብራዊያን 12፡1–2)

እስከ 1977 ዓ.ም. የተዘጉትና ከመዘጋት የተረፉት የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ስታትስቲክስ

ተራ ቁጥር	የአውራጃ ቤተ ክርስቲያናት	የአጥቢያዎች ብዛት	ያልተዘጉ አጥቢያዎች	የተዘጉ አጥቢያዎች
1	መላይታ	738	-	738
2	ከምባታና ሃዲያ (ዱራሜ)	300	300	-
3	ከምባታና ሃዲያ (ቦዚቾ)	260	260	-
4	ግሬቆ	6	-	6
5	ሰባት ቤት ጉራጌ (ጉመር)	5	5	-
6	ጨቦና ጉራጌ (መሊሶ)	8	1	7
7	ሣሸ (የም)	12	-	12
8	ጅግና ዙሪያው	15	13	2
9	አጋሮ	7	1	6
10	ቦንጋ	39	-	39
11	አሰብ	1	-	1
12	አሥመራ	1	-	1
13	ደቀመሐሪ	1	1	-
14	ደሴና ዙሪያው	3	-	3
15	ጅጅጋ	1	-	1
16	ባሌ	4	-	4
17	ጊኒር	1	1	-
18	የረርና ከረዩ	3	-	3
19	አዲስ አበባ	6	2	4
20	አርሲ	38	30	8
21	ሲራሮ	12	-	12
22	አዋሣ	4	-	4
23	ያናሴ	100	-	100
24	ጌዲኦ (ዲላ)	150	9	141
25	አለታ ወንዶ	177	-	177
26	ይርጋ ጨፌ	140	50	90
27	ጋጣ	12	10	2
28	አማሮ ኪሌ	27	3	24
29	ቡርጂ	7	4	3
30	ቋሚ	40	-	40
31	ጎፋ	250	50	200
32	ጨንቻ	142	1	141
33	ሐመር ባኮ	98	94	4
34	ዋካ (ኩሎ)	106	60	46
35	ጠደሌ	6	6	-
36	ድባጤ	4	2	2
	ጠቅላላ ድምር	2424	903	1521

1. ምንጭ፣ ጥር 2/1977 ከተረጋ የቢተ ክርስቲያኒቱ ሪፖርት፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጥና. ጽ/ቤት ዘና መጥፎ (በአቶ ጥላሁን ጎይሌ የተዘጋጀ) እና ከየአውራጃው ሪፖርት ጋር ተመሳክሮ።

2. ግብራሪያ፣

2.1 በመትት ያለተዘጉ በርኪታ ቤተ ክርስቲያናት በጎላ ተዘግተዋል። ከስደቱ ከብደት የተነሳ ትክክለኛ መረጃዎች ለማግኘት ወቅቱ ስለማይፈቅድ የአንዳንድ አጥቢያዎች የቁጥር መሩሰስ በረፀመጭ ምክንያት ይኖው ነው።

2.2 ከሁለት ዓመት በፊላ ነፈሰ 28/1979፣ በተረጋ አንድ ሪፖርት ላይ እንደተገለፀውና የአጥቢያዎች ብዛት 2983 ሲሆን የተዘጉት አጥቢያዎች ቁጥር 1536 ሲሆን ያለተዘጉት አጥቢያዎች ብዛት ደግሞ 1447 ይደርሱ ነበር።

ልማትና ርዳታ በስደቱ ዘመን

ስለ ታሪ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የልማትና ርዳታ አደግሙርና እንቅስቃሴ ለመተረክ ጥቂት ዓመታትን ወደ ኋላ ዞር ብሎ መመለከቱ አግባብ ነው። ልማቱና ርዳታው ሀገርንና ሕዝብን የሚመለከት ስለሆነ ታሪካዊ መነሻዎች ይመሳከራሉ። የኢሰአዴሓ ድርሻም ይወሳል። በእነዚህና መሰል ተጓዳኝ ሁኔታዎች ታሪኩ በሚጠቃቅሳቸው ሁነቶች የተንሰላስለው የቢተ ክርስቲያኒቱ የልማትና የርዳታ ሥራዎች ስዕል የሚከተለውን ይመስላል።

ለሁለተኛ ጊዜ ተቻቸሎ የተዘጋጀው የ1965 ዓ.ም የወንጌል አማኞች አንድነት ግጎበር መተዳደሪያ ደንብና አጽመ ሕግ በዘጠነኛው ዐብይ ርዕስ፣ «የግጎበሩ ጎላግ» በሚለው ክፍል ግጎበሩ የሚመራባቸውን ጎላግዎች በዝርዝር አስፍሯል። ለመነሻነትና በታሪካዊ ጠቀሜታነቱ አጋዥ ሊሆን ስለሚችል በአንቀጹ መሰየ የተዘረዘሩትን ጎላግዎች እናመላክታለን፣

ሀ. ት/ቤቶችን ማቋቋም
ለ. የሕክምና አገልግሎት መስጠት
ሐ. የመንፈሳዊያንን ማመለጠ ማቋቋም
መ. የልማት ዘርፎችን መዘርጋት
ሠ. ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን መስጠት

ረ. የበላ እድገትት ፕሮጀክት ማቋቋም ወይተ የመሳሰሉትን ሥራዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመተባበር ማከናወን።[180]

ከስድስቱ የግጎበሩ ዓላማዎች ተራ ቁጥር «ሐ» ብቻ ሲቀር የተቀሩት አምስት ዓላማዎች በሙሉ የሚያተኩሩት በልማትና ርዳታ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው። ይህም የሚያሳየው ተደጋ ካሉት ዓመታት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንጌል ሥራ ጎን ለጎን ለልማትና ርዳታ ሥራዎች ሰጥታው የነበረውን ከፍተኛ ትኩረት ነው። የሆነው ሆኖ የግጎበሩ ደንብ በተረቀቀበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ስላልተቋቋመ በደንቡ ውስጥ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማዎች ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ ሊሆኑ አልቻሉም።

በዚሁ በ1965 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ታሪክ መደር ያልተገኘለትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የረገፉበት የርሃብ መርዶ የተደመጠበት ዓመት ነው። ይሄው የርሃብ አለቲት እንደ ዋና ተጠቃሽ ምክንያት በመሆኑም ተደጋ ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ለመጥቀስ እንደሞከርነው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ ሊያከትም ችሏል።

በኢትዮጵያ የተከሰተው አሰቃቂ ርሃብ የንለምን ሕዝብ ስሜት ከዳር ዳር ጨምድዶ በያዘበት ወቅትና የለጋሽ ድርጅቶችና የሰብዓዊ ተቋማት የድረሱልኝ ጥሪ ከሀገሪቱ በተሰተጋባበት ጊዜ የኢትዮጵያው ኢሰአይኤም ለጥሪው የሰጠው ምላሽ ፈጣን ነበር። ሚሲዮኑ *R and R (Relief and Rehabilitation)* የርዳታና የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም በመንደፍ የርሃብ ጥቃቱ ባያለባቸው የክልቲማ፡ የመርሳ፡ የውርጌሳና የአላማጣ የርዳታ መስጭያ ማዕያዎች የምግብ ርዳታና የሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል።[181] በእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ በአብዛኛው የተሳተፉት ኢትዮጵያዊያን ሥራተኞች ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተውጣጡ ነበሩ። ከዚሁ የእርዳታና የመልሶ ማቋቋም ሥራ ጎን ለጎን ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተመረጡ መንፈሳዊያን የምሥራቹን ቃል ለማዳረስ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። በ1967 ዓ.ም. ደግሞ የፕሮግራም ማሻሻያ በማድረግ የጎብረተሰብ ልማት *(Community Development, CD)* በሚል ስያሜ ሚሲዮኑ ለአንድ ዓመት ተንተሳተሰ።

ይህ በዚህ እንዳለ ከየካቲት መር 1966 ዓ.ም. ጀምሮ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ማስተባበሪያ ቋሚራሮ ጽ/ቤት በደፋ ከተከፈተ

---

[180] በመንጌል አማኞች አንድነት ማህበር ቤቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት የተሳተ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ዓ.ም. አለተጠቀሰም ገጽ 1

[181] SIM Community Development Annual Report, Dec. 1975

ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ የአመራር አካላት ከመንፈሳዊው ሥራ ጎን ለጎን የልማትና ርዳታ ፕሮግራሞች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል።

በተለይም የአብዮቱ አካሄድ አቅጣጫ ያላግረው የኤስ.አይ.ኤም ሚሲዮን ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ያሉትን የቀለም ት/ቤቶች፥ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች ለመንግሥት ማስረከብ በመጀመሩ (በጊዜያዊነትም ቢሆን አን ዳንዶቹ ጣቢያዎች ይመሩ የነበረው በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነበር) በየአካባቢው ያሉት በርካታ ሚሲዮናዊያን ጣቢያዎችንና የርዳታ ማዕከሎችን እየተው እንዲወጡም ሚሲዮኑ ጥሪ አቀረበ።


የተሰባሰቡትም ሚሲዮናዊያን ከፊሉ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሲወሰን የተቀሩት ደግሞ ወደ ተለያዩ የአፍሪቃ ሀገሮች ለተመሳሳይ አገልግሎትና ተግባር እንዲሄዱ ተደረገ። ይህም ቢሆን ግን የምሥራቅ አፍሪቃው የኤስ.አይ.ኤም ቢሮ ሙሉ ለሙሉ ስላልተዘጋና እንደ ቢንግሃም አካዳሚና ዘነበ ወርቅ ሆስፒታል አካባቢ የሚገኘው የግተሚያ ግቢው ያሉት ተቋማት በሚሲዮኑ እጅ ስለነበሩ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ሚሲዮናዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ነበረባቸው። ለሚሲዮኑ የህልውና ድጋፍ እንዲሆን በእነዚያ ጥቂት ቁጥር ባላቸው ሚሲዮናዊያን አማካይነት በተወሰኑ የሶሻል መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ የገድ የማኅበራዊ ግልጋሎቶች መስጫ ፕሮግራም መዘርጋት ነበረበት። በዚህም ምክንያት በ1968 ዓ.ም «የቃለ ሕይወት ልማት አገልግሎት» *(Kale Hiywot Development Program, KHDP)* የሚለው ተቋም ሊመሠረት ግድ ሆነ። ይህንንም የልማት ፕሮግራም በበላይነት የሚመራ ቦርድ ሲቋቋም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም በቦርዱ ውስጥ አንድ ወንበር ተሰጥቷት አባል እንድትሆን ተጠየቀ። ነገር ግን በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስም የተቋቋመው ይህ የልማት ፕሮግራም የማንነት ጥያቄ ግልጽ ባለ ሁኔታ ስላልተጠቀሰና በቂ ማብራሪያ ሊሰጥበት ስላልተቻለ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጸሐፊ ራሳቸውን ከቦርዱ አባልነት በማግለል ወደፊት በቂ መልስ ሊሰጥበት የሚገባውን መሠረታዊ የባለቤትነት ጥያቄ መከራከሪያ በማቅረብ ጉባዔውን ተሰናበቱ።[182]

ይህ ሁኔታ በተፈጸመ በአጭር ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተሳተፈችበት የመጀመሪያው የሉዛን ጉባዔ በነሐሴ ወር 1968 ዓ.ም. በሲዊዘርላንድ ጄኔቫ ከተማ ይደረጋል።

---

[182] የአሥር ዓመት ተኩል የሥራ ሪፖርት፣ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣ የካቲት 1977 ዓ.ም.

በተባበሩት የዓለም ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት የተጠራው ይህ ስብሰባ እንደ ዶ/ር ቢሊግርሃምና ኤሲስ ቆጶስ ፌስቶ ኪቪንጀሪን የመሳሰሉ ታላላቅ የወንጌል ሰዎችና የሃይማኖት መሪዎች ተገኝተው ነበር።[183] ጉባዔው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከተወያየባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ፤ «ዛሬ ባለንበት የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለሦስተኛው ዓለም ድሃ ሕዝቦች በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልጋቸው ምንድን ነው? ወንጌል ወይንስ ዳቦ?» የሚል ነበር። ለጥያቄው ምላሽ እንዲሰጡ የተጠበቁት የአፍሪቃ የሃይማኖት መሪዎች ልባቸው በሀዘን ተመትቶ መልስ ከመስጠት ዝም ማለታቸውን ያስተዋሉት አውሮፓውያን ብድግ በማለት የሚከተለውን መልስ ይሰጣሉ። «ለራበው ሆድ በቅድሚያ መስጠት ያለብን ዳቦ ነው። ዳቦ ሥጋና ነፍስ አድን ነውና። ለራበው ሰው በዳቦ አማካይነት ነፍስ ከዘራንበት በኋላ ነው ወንጌልን ልንመሠክርለት የሚገባው።» በማለት ውይይት ከተደረገ በኋላ በርካታ የአፍሪቃ ሀገሮች የጎብረተሰባቸውንና የሕዝባቸውን የሥጋ ጥያቄ ለመመለስ አድማ ደካሞች መሆናቸው ተደጋግሞ ተወሳ።



በሱዛን ጉባዔ ላይ የተገኙት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ከከፊል የጉባዔው አባላት ጋር

[183] ዶ/ር ሙላቱ ባፋ፤ ቃለ መጠይቅ፤ የካቲት 1992 ዓ.ም.

ከእንግዲህ በኋላም በተለይ የአፍሪቃ ቤተ ክርስቲያን ለምታገለግለው ግጎበረሰብ ተገቢውን የልግትና የርዳታ አገልግሎት እንድትሰጥ አደራ ተላልፎ ጉባዔው ተዘጋ።

ተደጋ ሲል ለመጀመር የተሞክሩት የቤተ ክርስትያኒቱ ጠንካራ ጥረቶችና የጀኔቫው ጉባዔ እንደ መልካም ግላብ ተቆጥረው በ1969 ዓ.ም. የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር ቦርድ ጉባዔ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተጠናከረ የልግት አገልግሎት እንዲሰጥ ወሰነ። በዚሁ መሠረትም ከአንጻንድ ኢንተርናሽናል በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ከኤስኤይኤም ጋር በመተባበር በተመሰኑ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአመራጃ ጽ/ቤቶች አማካይነት በጎ ጅምሮች መከናወናቸው አልቀረም። ከእነዚህም ፕሮጀክቶች መካከል በጎጆ ኢንዱስትሪ፥ በአፈርና በውሃ ጥበቃ፥ በደን ልማት፥ በጓሮ አትክልት፥ በእርሻ መሣሪያ፥ በከብት፥ በዶሮና በዓሣ እርባታ፥ ወዘተ. የመሳሰሉትን ፕሮግራሞች በመዘርጋት አመራጃዎቹ በተቻላቸው አቅም ሁሉ አገልግሎታቸውን ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ ጎደላቸውን አስተካክለው ጥረት ለማድረግ ሞክረዋል።[184]

ለአብነት ያህልም በ1970 ዓ.ም. ሥራውን የጀመረው የጊዲኦ አመራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የልግት አገልግሎትን መጥቀስ ይቻላል። ከአገልግሎቱ መካከልም የቴመና ሥራ፥ የአናጢነት፥ የተርከሻና የቆዳ ሥራ፥ የሴቶች የባልትና ሙያ ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው። ሠልጣኞቹም የተመደቡበትን ሥልጠና በሚገባ ሲያጠናቅቁ ተገቢ የሆነው የትምህርት መረጃ ሰርተፊኬት ይሰጥ ነበር።[185]

የከምባታና ሃዲያ አመራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሰነዶችም የሚያረጋግጡት እውነታ ይኸንኑ ነው፤

በግንቦት መር 1969 ዓ.ም. ዶ/ር ሙላቱ ባሉና አቶ ተክሉ መ/ጊዮርጊስ አሰክ ጠዛ ዱራሜ ድረስ መጥተው ከአጋሬ ቀበሌ ግጎበርና ከተዲጳ ጋሜላ መሪጳ መንግሥታዊ የልግት ኮሚቴ ጋር የቤተ ክርስቲያኒቱን ተወካዮች ይዘው ተነጋገሩ። ተደጋ ሲል የአመራጃው ቤተ ክርስቲያን ለልግት ሥራ ተመርቶ የነበረውን ሩብ ጋሻ መሬት የጠዛ አጋሬ ክፍለ ግጎበር መስዶት የነበረውን ለልግት ሥራ እንዲሰጥ ተደርጎ የልግቱ ሥራ እንዲጀመር የመረጳው የልግት ኮሚቴ በጽሑፍ ፈቀደ።[186]

---

[184] የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባዔ 23/7/1976

[185] የጊዲኦ አመራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያልታተመ ከኖል ውስጥ

[186] ታምሩ አዳሞ፥ ቤተ ክርስቲያንና የልግት እንቅስቃሴ፥ ገጽ 85

በአጠቃላይ ሲታይ አንጋፋዎቹ የክርስቲያንና የሃያ ፡ የጊዲአን የወላይታ ታሪ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በአግት እን፡ ስታሊው አኳያ በአርአያነት የሚጠቀስ ተግባራት አከናውነዋል።

እንደ አቶ ደጉ ደቅላቦ ገለፃ ከሆነ በሐመር ባኮ አውራጃ ውስጥ የፍራፍሬ ተክሎችን (ማንኑ፡ ብርቱካን ወ.ዘ.ተ.) ሕዝቡ እያመረተ እንዲጠቀም ያስተዋወቀችው የታሪ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። የፍራፍሬ ዛፎችን ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ የአመጋገብ ባህልና የምግብ አበሳሰል ሥርዓት ለውጥ ላይ ቤተ ክርስቲያኒቱ የተጫወተችው ሚናና ያስከተለችው ለውጥም እጅግ ከፍተኛ እንደነበር በስፋት ተመስክሏል።[187]

የታሪ ሕይወት ቤተ ክርስትያን በአብዛኞቹ የአውራጃ ቤተ ክርስትያናት አስተባባሪነት በአውራጃዎቿ ውስጥ የተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ስታደርግ የኤስኤዲኤ ሚሊዮንም፣ «የታሪ ሕይወት የልማት አገልግሎት» በሚል ተመሳሳይ ስያሜ ተጓዳኝ ሥራዎችን እየሠራ ባለበት ወቅት አብዮቱ ከዕለት ወደ ዕለት ቤተ ክርስቲያንን በጠላትነት ዓይን እያየ የጥፋት እጁን መጀርጋት ጀመረ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተዘጉ። ብዙ ቅዱሳን ታሠሩ። በቤተ ክርስቲያን ላይ «መጪ ሃይማኖት» የሚል ቅጥያ ተለጠፈባት። የሚሊዮን ተጃግትም፣ «የአሜሪካ የስለላ ድርጅት፡ የሲአይኤ ዋነኛ ድርጅቶች» እንደሆኑ ተደርጎ ይታመን ጀመር። በዚህም ምክንያት የሀገርኛ ቤተ ክርስቲያናት ደጃፎች እየተቆለፉ ምዕመኑ ወደ መሀረ ሲመረመር፡ ሚሊዮኑ ያከናውናቸው የነበሩ ልማቶችም እየተዘጉና እየተመረሱ ሚሊዮናውያኑ ከሀገር መውጣት ጀመሩ።

የጨለማው ወቅት እየከበደ፡ የመከራው ዶፍ እየዘነበ በመሄዱ ሁኔታዎች ሁሉ በመጨናገጋቸው ይፋዊ የሆነ የመንጌል ሥራም ሆነ የልማትና የርዳታ እንቅስቃሴዎች እንደ አብዮቱ ደመኛ የሚቆጠሩበት ደረጃ ላይ ተደረሰ። በተለይም በ1976 ዓ.ም የመታደራዊው ደርግ ለ10ኛው የአብዮት በዓልና ለኮሚኒስት ፓርቲው ምሥረታ በሙሉ ኃይሉ ሽር ጉድ የሚልበት ዓመት ስለነበረ ከአብዮት ቋንቋ ሌላ፡ «ስለ ሃይማኖትና ስለ ሚሊዮን ድርጅት» መናገር በራሱ ከፍተኛ መንጀል ነበር። መፈክሩና ቅስቀሳው በሙሉ «ጠላቶቻችንንም ሆነ ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን!» የሚል ብቻ ሆነ። ከኮሚኒስት ሀገሮች ውጭ ያሉ ግናቸውም ምዕራባዊ ሀገሮች በሙሉ ለሶሻሊዝም ሥርዓት ጠንቀኛ የሆኑ ኢምፔሪያሊስቶች እየተባሉ ተወገዙ። ዋና ዋና ከተማዎች

---

[187] አቶ ደጉ ደቅላቦ፣ መጋቢት 27/1991 ዓ.ም.

የኮሚኒስት ፓርቲውን መመለድ ሊያበስሩ ልዩ ልዩ ቀለማት ባላቸው አምጭሎች አሸበረቁ። ቁጥራቸው 54,000 የሚሆኑ የአዲስ አበባ ወጣቶችና ሠራተኞች የአብዮት በዓሉንና እንግዳውን ፓርቲ በሠልፍ ሊቀበሉ ትምህርቱና ምርቱ ቀርቶ ለሰልፍ ትርዒቱ «ግራ ቀኝ» እያሉ መለማመድ ሥራቸው ሆነ። ሰልፈኞቹ በሰልፍ ትርዒቱ መሃል እየጮሁ የሚሉት መፈክር ተዘጋጅቶላቸዋል። ግማሹ፤ «ጓድ መንግሥቱ! . . . » ሲል ከፊሉ ደግሞ፤ ኃይለ . . . » በማለት ያስተጋባል። የተቀሩት፤ «ማርያም . . . » በማለት የአብዮት አደባባዩን ባለ በሌለ ኃይል በጩኸት እንዲያደበላልቁት ይጠበቃል። ሰልፈኛውን ቀድመውና ተከትለው በትርዒቱ የሚያደምቁ ህፃናትም ተዘጋጅተዋል። በርዕሰ መዲናዋ በአዲስ አበባ ውስጥ ጎዳናዎችን ሞልተው የሚታዩት የሰሜን ኮሪያ ጓዶችና የወዳጅ ሀገሮች ዜጋዎች ብቻ ሆኑ። ድርሻቸው መፈክሮችንና በመብራት የተንቆጠቆጡ የከተማ ማስዋቢያዎችን ማደራጀት ነበር።



የ1977 ዓ.ም. የድርቅ አሻራ

ይህ በዚህ እንዳለ የዳር ሀገሩ ወገን ግን በርሃብ እየረገፈ ነበር። ብዙ ወገኖቻችን የርሃቡን መቅሰፍት ለመሸሽ ቀኤያቸውን እየለቀቁ ወደ ከተማ መጉረፍ ጀመሩ። የከተማ ኪላ ጠባቂዎች ደግሞ እያፈሱ ወደ ማጎሪያ ጣቢያዎች ያግዟቸው ጀመር። ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሰማኒያኛ ዓመት የልደት በዓላቸውን እያከበሩ በነበረበት ወቅት ከተከሰተው የርሃብ እልቂት ይልቅ ደርግ የአሥረኛ የአብዮት በዓሉን ለማክበር ሽር ጉድ



የ1977 ዓ.ም. የድርቅ አሻራ

ሲል፤ «የዝሆን ጆሮ ይሰጠኝ» በማለቱ የተከሰተው ረሃብና ድርቅ አይሎ መግዘፉ በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ የዜና አውታሮች ይስተጋባ ጀመር። በሰሜኑ ክፍል ያሉት ወንዞችና ኩሬዎች ደረቁ። የሰደድ እሳት በየቦታው ተነሳ። የተበተነው ዘር ገና ብቅ ሲል እየከሰመ ደረቀ። የገበሬው ለም ማሳ ወደ አቧራነት ተለወጠ። ዘላን ወገኖቻችን ውሃ ፍለጋ ከሀገር ሀገር ተንከራተቱ። ከብቶችና የቤት እንስሳት እንደ ቅጠል ረገፉ። ችግሩና መደናገጡ ከሀገር አቀፍ ደረጃ አልፎ ከዓለም ሕዝብ ጆሮ ደረሰ። ዶ/ር ፒተር ኮትሬል ሁኔታውን እንዲህ ይገልጡታል፤

በ1975/76 ዓ.ም. የተከሰተው የርሃብና የድርቅ አደጋ በ1965/66 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከደረሰውና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን እንዲወርዱ ምክንያት ከሆነው የርሃብ ክስተት ይልቅ በእጅጉ የከፋ ነበር። ይበልጥ የከፋ ነበር ከተባለም እ.ኤ.አ. ከ1889–1892 በኢትዮጵያ ተከስቶ ከነበረው የታሳቁ የርሃብ ዓመታት ይልቅ በእጅጉ የላቀ ነበር። ርሃቡ በተስፋፋበት አካባቢ ይኖሩ የነበሩት 80% ያህል ነዋሪዎች እንደ ቅጠል ረግፈዋል። ርሃቡ ያጠቃው ተደጋግሞ እንደሚነገረው ሰሜናዊውን የሀገሪቱን ክፍል ብቻ ሳይሆን ድቡቡንም፥ ምሥራቁንም፥ ምዕራቡንም የሀገሪቱን ክፍሎች በጠቅላላው አዳርሶ ነበር።[188]

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከመውረዳቸው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ለመጨረሻ ጊዜ ነሐሴ 23/1966 ዓ.ም. «ሞአ አንበሳ ዘዕምነ ነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» የሚለውን ማኅተማቸውን በማሳረፍ በአዋጅ መቋቋሙን ያበሰሩለት የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የሚይዘውና የሚጨብጠው ጠፍቶት ከላይ ታች ባዘነ። ፊቱን ወደ ሶሻሊስት ሀገሮች አዙሮ የነፍስ ያለህ ቢልም ሰሚ አጣ።

ልመናዎቻችን ተቀባይነት አላገኙም። ግንም ርዳታ ሰጪ ሁኔታው እንደጠየቀው አፋጣኝ መልስ አልሰጠም። ወዳጆቻችን የምሥራቅ ክፍሎች ሞርሱኑ ችላ አሉን። ብዙዎች በምንከተለው የማርክሲስት መንግሥት ላይ ጥላቻቸውን ለመግለጥ ጀርባቸውን ሰጡን።[189] በማለት የወቅቱ የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩት ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ በግለ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ እውነቱን ገልጸዋል። የታለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በተስፋፋችባቸው በወላይታ፥ በከምባታና

---

[188] Peter Cotterell, Cry Ethiopia, MARC: Eastbourne, 1988, P. 145

[189] ደበበ እሸቱ ተርጓሚ፣ ገጽ 162

ሃዲያ፥ በሰሜንና በደቡብ ኦሞ የሚገኙት አካባቢዎችም ለርሃቡ አደጋ እጅጉን ተጋልጠው አደጋ ላይ ወደቁ።

«የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይተላመጡ» እንዲሉ የደርግ መንግሥት የምሥራቅ አውሮፓ ወዳጆቹ ሬት ሲነሱት የልመና እጁን ወደ ምዕራባውያን ሀገሮች መዘርጋት ጀመረ። በዚህ ወቅት ነበር ህዝቡ፣ «የጦር መግሪያ ከምሥራቅ የፅለት ጉርስ ከምዕራብ» በግለት ትዝብቱን መግለፅ የጀመረው። ርግቡ የጠናበት ሰሜንኛው ሕዝብም እንዲሁ ብሶቱን፥ የውስጥ ስሜቱንና የቆሽት መድበኑን ሕመም ይገልፅ የነበረው በተለያዩ ሥነ-ቃል (ሕዝባዊ ግጥሞች) አማካይነት ነበር። እነዚህ ህዝባዊ ግጥሞች በአንድ አካባቢ ብቻ የተነገሩ ሳይሆኑ ሁሉም በየቀኤው በቋንቋው ያንጎራጉረባቸው ናቸው። በመሆኑም በ1977 ዓ.ም. ለተከሰተው አሰቃቂ ርግብ በተለይም የሰሜን ሽዋ አካባቢ ጉዳተኛ ሕዝብ ትዝብቱን፥ ምሬቱን፥ ህዘኑንና ጉስቁልናውን ከገለጸባቸው ሕዝባዊ ግጥሞች መካከል የሚከተሉትን ብቻ መርጠን መስደናል።

• አዩ ለዛ ለዛት፥ አዩ ቸንፈሩ፥
እህል መብላል ተርቶ፥ እንጦጠ አፈሩ።

• ብፈጠው ቦንብ
ሞኳው ተመክ!
ብፈጣረው ግብ!
አዩ ለዛ ለዛት ያሰብህ አበላ።

• የዘንድሮው ነገርን አግርኛው ጠፍቶ፥
ግረኛ በአንድ ቋር፥ ጠብመንጃ በመቶ።

• ለዛ ለዛት ዘመን፥ ይቅር አይባል፥
እርጉዝ ላሜን ጀኖኳት ለሁለት ቀን ምግ።

• እንኳን በአንድ ምጥድ ቢጋር በመቶ፥
«ደጀችንጋ ቅመቷ» ምነው ደሮ ተርፉ።

• አህል ታጧል አለ፥ ጀርን እንየው፥
ቦግደርን እንደሆን እኛ እንትደመው።

• ያንን ለዛ ለዛት፥ አሰሩት በገመድ፥
መደ ለዛ ሰምንት፥ መደ ለዛ ዘጠኝ እንዳደረግመድ።

• ይሄ ለዛ ለዛት፥ ምንው ጠለመብኝ?
ቀኑም ሆነ ሌቱ አንድ አየሆነብኝ።

• ሰላ ለሳት፣ የዜንቶን ይት ዘጋ፣
ያልሰሙ የዜም ልብሁን ያልዘረጋ።

• ከዚት ረዘሬል አሉ፣ በለባ ለሳት፣
የሚሽሙ ጠፍቶ ዝሆ ሊዎት።

• እግዚአብሔር ይደልህ አያ ለባ ለሳት
ልጀ ትመሳሽ አናጀ ምታሳት።

• ከብቶቼን ጠርዜ፣ ልጀን ላስግግ
ተይ መቱተል ብት አለ፣ በትልቱ ተግ።

• እኩም አያመሳን፣ እኛም አናመታችሁ፣
በመርዝብ መጣ፣ አሳነን ስንዲአችሁ።

• በለባ ለሳት፣ የመረጀው እንሳ፣
መረቱን አተግ፣ አበሳስ ተልሳ

• ለሳ ለሳት ንብቶ የተመልሳችሁ፣
አህል አትድረሩ ጠሳብ ኑው ሆሳችሁ።

(የንጉሥ ምንጭ፣ Fekede Azazu, Dr. Un Heard Voices. 1998)

እነዚህ ሕዝባዊ ግጥሞች የያዙት መልእክት ከብዙ የምሁራን ትንተና ይልቅ ስሜትን ዘልተው የሚነኩ ስለሆነና ዜመኑን በሚገባ ስለሚያሳዩ ተገቢው ቦታ ሊሰጣቸው ግድ ሆኗል።

ለርግቡና ለድርቁ መረርሽኝ ችግር መፍትሔ መስጠት አትቷት ገራ የገባው ኮሚኒስቱ የደርግ መንግሥት የግታ ግታ ከ5–6 ሚሊዮን ለሚገመተውና በርሃብ እየረገፈ ላለው መገናኝን ፈጥነው እንዲታደጉ እፍረቱን የዋ አድርጎ ጠላት ሲላቸው ለነበሩት ለምዕራባውያን ሀገሮች የድረሱልኝ ጩኼትን አስተላለፈ። መልዕክቱ የተላለፈላቸው የምዕራቡ ገራ መንግሥታት፣ የሰብዓዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና የታወቁ ግለሰቦች የሰጡትን ምላሽ በተመለከተ የወጡት የርዳታና ማስተባበሪያ ኮሚሽነር ጳሮት መ/ጊዮርጊስ እንዲህ ይገልፁታል

በድንገት ሊትዮጵያ የምትዘነጋ ሀገር ሆነች። የተከሰሩ የፖለቲካ ለምኝ፣ ተዋንያን፣ . . . የዜተ ከርሱቲያን መሪዎች፣ የሰብዓዊ አገልግሎት ተጠሪዎች፣ ተራ ለምኝ ከግለም አትዜል ሁሉ፣ ይህንን የዘመትን አልቂት በዐታው ተገኝተው ለመመልከት ጎረፉ። አንዳንዶች አየጅ አየተንገረፉቸው ሌሎች መዎግታቸው ላይሰማ፣ ዜሙ ለረዳቸው ጥቅና ለፖለቲካ አቋማቸው ግሬጋጭ አንዳንዶች ለጅብየንነት፣ ዜሙ ደግሞ በውኔታው

በመነካትና በህዘኔታ ነበር አመጣጣቸው። . . . አየር ማረፊያ ዕታ በሜኑ አውሮፕላናች . . ጋዜጠኞች ለሚመጡትና ለሚሄዱት ታለ መጠይቅ ለማድረግ ታዋቂ ሰዎችን ይጠብቃሉ።[190]

ከተጠቀሱት ታዋቂ ሰዎች መካከል የአለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት፥ የተለያዩ መንግሥታት የልማትና የእርዳታ ድርጅቶች ተወካዮች፥ የተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣናች፥ ሴናተሮች፥ ጠቅላይ ሚኒስቴሮች፥ የልዩ ልዩ ሀገሮች የፓርላማ አባላት፥ በርካታ የሚሲዮን ድርጅቶች፥ የቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ወዘተ. ይገኙበታል።

ይህንን መሰሉን አጋጣሚ በመጠቀምም ብዙ ሚሲዮናዊያንን ቀደም ሲል ከሀገር ያስወጣው የኤስኤይኤም ሚሲዮንም በኢትዮጵያ ውስጥ በተስፋ መቁረጥ የጨለገውን ዓይኑን ለተሻለ ራዕይ መክፈት ጀመረ። የዛለውን ጉልበቱን በማጠናከር እንደገና ተነቃቅቶ ወደ ህዝቡ የሚደርስበትን የርዳታ ጎዳና ጥርጊያ ማመቻቸት ጀመረ።

ብራያን ፋርገር የተባሉ አንጋፋ የኤስኤይኤም ሚሲዮን ያንን ዘመን ርሃብና የርዳታ ጥሪ በተመለከተ የሚሲዮኑን ምላሽ በግልፅነትና በዝርዝር እንደሚከተለው ይገልፁታል፣

«ልማት»ን እንደ ልዩ ሲሳይ አምጭ (fairy godmother)ስለ ቆጠረው የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ሀገር ርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን፥ ኤስኤይኤምን ጨምሮ የተለያዩ የሚሲዮን ተቋማትን የተቀበለው እጅን ዘርግቶ ነው። የልማት ፕሮጀክቶችን ዝርዝር ጥናት ለማቅረብ የቻለና ከጎብረተሰቡና ከአካባቢ ባለሥልጣናት አሽታ ማግኘት ከተቻለ ግዕከላዊ መንግሥት ፈቃድ ለመስጠት አላመነታም። ፈቃድ መስጠት ብቻ ሳይሆን በተፈለገው ቁጥር መጠን ተፈላጊ የሆኑትን የውጭ ሀገር ሰዎችንም ለማስገባት ጥምር ሁኔታዎች የተመቻቹ ነበሩ። በዚህ አጋጣሚም ቀደም ሲሉ ወጥተው የነበሩ የኤስኤይኤም ሚሲዮናዊያን በመምህርነትና በህክምና ሠራተኝነት ሰም ወደ ኢትዮጵያ የመመለሱ እድል ተከፈተላቸው። እንደ ፋርው የእርዳታ ሥራውም እንዲሁ የተመቻቸ ነበር። በመላው ሀገሪቱ ተሰፋፍቶ በነበረው ድርቅ ምክንያት ብዙዎቹ የውጭ ሀገር ዜጎች፣ ላንዱ ለመስፈርናው የተረጂዎቹን የጉዳት ልክ ለማወቅ በአካል እየተገኙ ያገጠጠውን የርሃብተኞች ጎን ለመቋጠር ተመግሩ። ገንዘብ ይዘው ከመጡ ሥራና የሥራ ፈቃድ አይጠፋም ነበር። ሰለዚህም ለግትና እርዳታ በሀሩር አካባቢ እንደተገኘ ቀዝቃዛ አየርና ውሃ የውጭ ሀገር ሰዎችን ማርካት ጀመረ።[191]

---

[190] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 217

[191] Brian Fargher, PP. 306-307

ይህንን «መርኃግ ዕድል» ለመጠቀም የኤስ.አይ.ኤም ሚሲዮን ጊዜ አልፈጀበትም። ከከፍተኛ ቁጥር ሚሲዮናዊያን ወደ ኢትዮጵያ ይጎርፉ ጀመር።

«የቃለ ሕይወት የልማት ድርጅት» የሚለውንና ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀመበት የነበረውን ስያሜ ከፍ አድርጎ በተከፈተው የዕድል በር እንደልቡ መውጣትና መግባት ሲጀምር ከጥቂት ዓመት በፊት የልማቱን ስያሜ በተመለከተ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የተነሳው፤ «የቃለ ሕይወት የልማት ድርጅት» የሚለውን የስሜን መልስልኝ ጥያቄ ነፍስ እየዘራ መጣ። የአሁኑ ጥያቄ የተነሳው በቂና አሳማኝ ምክንያቶችን ይዞ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ መጋቢት 23/1976 ዓ.ም የተሰበሰበው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር ቦርድ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ የልማት አገልግሎት የሚከተለውን ወሰነ፤

ከዚህ ቀደም የቃለ ሕይወት ልማት አገልግሎት ፕሮግራም በመባል ታውቆ ሲሰራ የነበረው የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥራ ዘርፍ ከዛሬ ከመጋቢት 23/1976 ዓ.ም ጀምሮ ለአሠራርና ለአደረጃጀም እንዲያመች ዘንድ «የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ልማት አገልግሎት» (ቃሕቤልአ) በሚል ስያሜ ታውቆ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሠረት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ከአርዳታ ግስተባባሪያና ግደቋሚያ ኮሚሽን መሥሪያ ቤት ጋር የውል ስምምነቱን ተፈራርሞ የርዳታና የልማት ፕሮጀክቶች ዘርፍ እንዲያሰፋፋ እንዲደረግ።[192]


በዚሁ መሠረትም የመቅቱ የኤስ.አይ.ኤም ሚሲዮን ድርጅት ዋና ዲሬክተር ሚ/ር አሌክስ ፈሉስ ውግኔው በቦርዱ በተሰጠ ዕለት በጉባዔው ላይ ተገኝተው ስለአበር የቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ለቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲመለስና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሚሲዮኑ የራሱን ስያሜ ፈጥሮ በተገኘው እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ተገለጸላችው። ተገቢው የመንግሥት አካል ውግኔውን እንዲያውቀውም ተደረገ።

ኤስ.አይ.ኤም ሚሲዮንም በውሳኔው በመስማማት አሥር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የራሱን የልማት ዘርፍ ስያሜ ለአራተኛ ጊዜ አሻሽሎ «ሶሳይቲ ኦፍ ኢንተርናሽናል ሚሽነሪስ ኮሚዩኒቲ ዲቬሎፕመንት» በአፅርኦተ ቃል «ሲም ኤይድ» (SIM-Aid) በማለት አገልግሎቱን ቀጠለ።

---

[192] የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቦርድ ቃል ጉባኤ መጋቢት 23/1976 ዓ.ም.

የታለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ከሐምሌ 11/1976 ዓ.ም. ጀምሮ የወትቱን የቤተ ክርስትያን ሊቀመንበር አቶ ሙላቱ ታዬንና ዋና ጸሐፊውን አቶ ተክሌ መ/ጊዮርጊስን መክላ ከርዳታ ማቋቋሚያና ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር ከነበሩት ከሻለቃ ዳኛት መልዶ ጊዮርጊስ ጋር በመፈራረም በስጂ የሰየመችው የልማት አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ መቋቋሙን አበሰረች።



2. Any action required or permitted to be taken, and any documents required or permitted to be executed under this Agreement on behalf of the Commission may be taken by any of the Commissioners or any such other person or persons as they may designate in writing.

3. This Agreement shall be executed along with its Plan of Operations and Accounts Manuals.

4. Any notice or request made under this Agreement shall be deemed to have been duly given or made when it is delivered by hand or advanced by mail to the other party at specified hereunder.

IN WITNESS WHEREOF, the parties hereto, acting through their representatives thereto duly authorized, have hereby affixed their respective seals and signatures.

FOR THE COMMISSION

FOR AND ON BEHALF OF THE ORGANIZATION

Takla B.Giyorgis

General Secretary

11/11/76

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት ጋር የተፈራረመችበት የመጀመሪያው ሰነድ፣ ገጽ 9

የልማትና የርዳታ ፕሮግራሙን እንዲያስተባብሩም በኃላፊነት አቶ ንጉሤ ዘውዴን በመቅጠር በከፍተኛ ደረጃ እንቅስቃሴዋን ተጠለችች። በዚህ ወቅት ከ30 በላይ የሆኑ የአርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለታለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ትብብር አድርገዋል። ድርጅቶቹም በአብዛኛው በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካና በአውስትራሊያ ይሠሩ የነበሩ ናቸው። የአርዳታ ቁሳቁስ ተረፈ ግለት ይቻላል።[193]

---

[193] ንጉሤ ዘውዴ፣ የግል ማስታወሻ፣ 08/08/91 ዓ.ም.

ይህ የልማትና የርዳታ አገልግሎት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በሺህ የሚቆጠሩ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች የተዘጉበት ወቅት ስለነበር እንደልብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ሁኔታዎች የሚያመቹ አልነበሩም። እንደተጠበቀውም ልማቱ ወደ ተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት ለመቅረብ ትልቅ በር ከፍቷል። ወደ ተፈለገበት የሀገሪቱ ክፍሎችም እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ ተችሏል።

የተዘጉ የቤተ ክርስቲያናት ሽቢዎች በልማት ስም እየተከፈቱ የልማት ቢሮዎች ሆኑ። የቤተ ክርስቲያናቱ መሪዎችም የልማትና የርዳታ ሥራዎችን በማስመልከት ከመንግሥት አካላት ጋር መደራደር ቻሉ። ለበርካታ አካባቢዎች የልማት ሥራና የርዳታ አገልግሎቱ እንደ አንድ የመንግሥት አጋዥ ኃይል ሆኖ መታየት ጀመረ። እያደርም በየአካባቢው የወንጌል ሥራ በነፃነት ይካሄድ ጀመር።

በየአቅጣጫው በተከፈተው ሰፊ የአገልግሎት በር በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ዶ/ር ሙላቱ ባፋ ቤተ ክርስቲያኒቱን በሊቀመንበርነት ለስድስት ዓመታት ከመሩ በኋላ በኤስ.አይ.ኤም ውስጥ የነበራቸውን የልማት ሥራ ሀላፊነት በመልቀቅ ከመስከረም 25/1977 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ እንዲሆኑና አቶ ተክሌ ወ/ጊዮርጊስም የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ ሆነው እንዲያገለግሉ ተወሰነ።

ሥራው እየሰፋ ሄደ። የተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት የመከፈት ዜና አንድ በአንድ እየተደመጠ መጣ። ጥቂት ምዕመን ብቻ የነበራቸው አብያተ ክርስቲያናት የተዘጋው የጸሎት ቤታቸው ዳግመኛ ተከፍቶ ፕሮግራም ማካሄድ ሲጀምሩ በአሥር እጥፍ በዝተው ታዩ። ቀደም ባሉት ዓመታት በለስላሳ ቅላፄ ይዘመሩ የነበሩት የትርጉም መዝሙሮች በሀገርኛና በራስ ቋንቋ በሚዘመሩ አስደናቂ ዜማዎች ተተኩ። ልማትና ርዳታን ተጠልለው የተከፈቱት አብያተ ክርስቲያናትም የሁሉም ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ልማት ነው ብለው በተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እስኪደርሱ ድረስ «ያለ ልማት . . . » ማለት ጀመሩ።

ከመከራው በፊት በራስ እውቀትና ገንዘብ መንፈሳዊ አገልግሎቶችንና ልማትን ያንቀሳቅሱ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው ሲከፈቱ ያለ ልማትና ርዳታ የድጋፍ ምርኩዝ ራሳቸውን ችለው መቆም ተሳናቸው።

የልማትና ርዳታ ፕሮግራም አብያተ ክርስቲያናትን ዳግመኛ ለአደባባይ የግብቃቱ ክስተት መልካም ቢሆንም በአንጻሩ ግን ደባል

የሆኑና የአመጋገብ ባሕልን የተጻረሩ ገጠመኞችን ወደ ቤተ ክርስቲያናትና ወደ ችግረኛው ተጠቃሚ ሕዝብ ዘንድ ማስረጹ አልቀረም።

አበው፤ «የስጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም» ብለው እንደ ሚተርቱት ሁሉ በአብዛኛው በርዳታ መልክ የገቡት የምግብ ዓይነቶች ከሕዝባችን የአመጋገብ ሥርዓትና ወግ ጋር የሚሄዱ ዓይነት ስላልነበሩ ለረጂዋ ቤተ ክርስቲያን ካተረፉላት መልካም ስም ይልቅ የስድብ ቅጽሉ በረከተ። «ክስንዴ ጋር የመጣ ሃይማኖት፥ በብስኩት የሚደለሉ አማኞች፥ ሰልቫጅ ሃይማኖት . . .» የሚሉቱ ስድቦች መንስዔና ምንጩም ይሄው ሆነ።

ሌላው የልማትና የርዳታ ደካማ ጎን በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥና በህዝቧ መካከል የተረጂነትና የተመጽዋችነት ስሜት ማስረጹ ነው። ይህ የተረጂነት ስሜት በቤተ ክርስቲያን ሕዝብ እጅ ያለውን እምቅ ሃብትና ኃይል ለማስተዋል እንዳይቻል የሚጋርድ ዓይነ ርግብ ሆኗል። ራስን በራስ ለሚያስችል ዘላቂ የልማት ፍሬ ከመሥራት ይልቅ በጊዜያዊ ርዳታ የመደለል ልማድ ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ መሄድ ጀመረ።

የመጀመሪያ አባቶች እርስ በእርስ በመረዳዳትና በመደጋገፍ በራሳቸው ገንዘብ ወንጌላዊያንን ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ያሰማሩ ነበር። የዘመነ አብዮቱ የርዳታ ልምምድ ግን በራስ ሃብትና እቅድ ላለመንቀሳቀስ እንደ ሰንሰለት አስሮ አላላውስ አለ።

በልማትና በርዳታ ላይ የተሠማሩ በርካታ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለሥጋ ፈተናና ለጊዜያዊ ጥቅም በመሸነፍ አደራቸውን ጣሉ። ከስህተታችሁ ተመለሱ ብሎ የሚመክራቸውንም ለማጥቃትና የቤተ ክርስቲያንን ጎብረት ለማናጋት ተበረታቱ።

ረጂ ድርጅቶችም በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከመፍጠር ይልቅ የበላይነት ስሜትንና የረጂነት ብቃታቸውን በግንጻባረቅ እነርሱ የበላይ፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የበታች እንደሆነችም ለማሰብ ዳር ዳር ማለት ጀመሩ። ልማቱና ርዳታው የጠቀመውን ያህል የሚጎዳውና የሚያጠፋው እየበለጠ ሄደ።


ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀደም ሲል በልማት አገልግሎት ሰፊ ልምድ ቢኖራትም የሰውን ሁለንተና *(Holistic Ministry)* በግልገሉ አንጻርና የልማት ሚና ከመንፈሳዊው አገልግሎት ጋር እንዴት ተጣምሮ ሊሰጥ እንደሚገባው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቀዳሚነት ትምህርት ባለመስጠቱና ዝግጅት ባለመደረጉ ችግሮቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎሉ መምጣቸው አልቀረም። የቤተ ክርስቲያኒቱ የልማት አገልግሎት መምሪያ

ኃላፊ የሆኑት አቶ ንጉሤ ዘውዴ በአንድ ወቅት ባዘጋጁት የጥናት መረቀት ላይ የተጠቀሙበት ምሳሌያዊ ገለፃ በልማቱና በርዳታው ምክንያት ተሳቦ የመጣውን አደጋ ቁልጭ አድርጎ የማሳየት ብርታት ስላለው የአቶ ንጉሤ ዘውዴ ምሳሌያዊ ገለጻ እንደሚከተለው ተመጥኖ ተወስዷል።

ስለ አዞ ሲነሳ በዚሁ በሀገራችን ያሉ ሁለት የተለያዩ ቦታዎችን ማስታወስ ይቻላል። የመጀመሪያው በሜሞ ሐይቅ ዙሪያ የሚገኘው ተፈጥሯዊው የአዞ ገበያ ሲሆን ሁለተኛው በአርባ ምንጭ ከተማ የሚገኘው ሰው ሰራሹ የአዞ ርባታ ጣቢያ ነው። አዞ ገበያ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚኖሩ አዞዎች የሚኖሩት በነፃነት ነው። ምግባቸውና ዕድሜያቸው በሰው ልጆች ፈቃድ አልተገደበም። ቢርባቸው መደፈሰጉት ቦታ በመንቀሳቀስ አድነው ይበላሉ። በሰው ሰራሹ የአዞ እርባታ ውስጥ የሚኖሩት ግን እንቅስቃሴያቸው በሙሉ በሰው ልጆች ፈቃድ የተገደበ ነው። ኑሮአቸው የእስራት ያህል ይከብዳል። የሚሰጣቸው ምግብ በሰው እጅ እየተመጠነ ነው። በተሠራላቸው ትንሽ ኩሬ ውስጥ ይኖራሉ። ውሃው በየጊዜው ቢቀየርም የሚቆሽሸው ቶሎ ቶሎ ነው። ምርጫ ስለሌላቸው ይኖሩበታል።



አርባ ምንጭ የሚገኘው ሰው ሰራሹ የአዞ ርባታ ጣቢያ ከፊል ገጽታ



አርባ ምንጭ የሚገኘው ሰው ሰራሹ የአዞ ርባታ ጣቢያ ከፊል ገጽታ

እነዚህ አዞዎች ገራምና የተመቻቸው ቢመስሉም እውነታው ግን እንደዚያ አይደለም። አንዳንዱ የሚታመሱት ምግብ ሲወረወርላቸው ብጥብጥና ሁከት ይፈጥራሉ። ጠንካራው ደካማውን እየተጫነ በብል ጠቱና በጉልበቱ እያሸነፈ ከሚወረወረው ምግብ ቀዳሚ ተጠቃሚ ለመሆን የተቻለውን ትግል ያደርጋል። ሌላው ደግሞ የተወረወረውን ምግብ አገኘሁ ብሎ አንዱ አዞ የሌላኛውን የጓደኛውን አዞ ጭራ፥ ወይንም የሌላኛውን እግር ይይዛል። በአዞ ጥርስ ውስጥ መግባት ደግሞ ለአዞዎቹ ለራሳቸው ውጤቱ የከፋ ስለሚሆን አንዱ አዞ የሌላውን ወዳጁን ጭራ ወይንም እግር ቆርጦ ይበላል። በመጨረሻም የሁሉንም ለስላሳ ቆዳ ገፎ ለመውሰድ ሲባል አርቢዎቻቸው ያርዱቸዋል።

ይህ ምሳሌያዊ አገላለጽ በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን የልማትና የርዳታ አደጋ ጠቋሚ ነው። ሕዝባችን ሰፊውንና ተዝቆ የማያልቀውን በእጁ ያለውን ሃብቱን በመርሳት ወይንም ባለመፈለግ በጠባብ ዓንኳ የሚንጠባጠብውን የርዳታ ጠብታ ለመቃመስ እርስ በርሱ ሲበጣበጥና ሰላም ሲያጣ ይስተዋላል። ይህን መሰሉ ሁኔታ የሚያመጣው ደግሞ የማታ ማታ ለአጥፊውና ለበላተኛው ጠላት ለዲያብሎስ ነው።[194]

ተፋቅረውና ተጠጋግተው በፍቅር አብረው በመቻቻል ሲሰሩ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ግንበራት፤ «ልማት»ን እንደ ምክንያት በመቁጠርና የጠብ መነሾ በማድረግ ሆድ ለሆድ ተሸካከሩ። በትንሳኤ እየሮጡ ወንጌሉን ያርጡ የነበሩ በርካታ ትጉሃን የወንጌሉን ሥራ እየተው በልማት ሥራ ውስጥ ግገልገል በመጀመራቸው ተደነቃቅፈው ቤተ ክርስቲያንን ያደነቃቅፉ ጀመር። ተጠያቂነቱም ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መጣ።

«ልማት» ለቤተ ክርስቲያን፤ "ላም አሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈሯት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት" እንዲሉ የተገለጸ ችግርና የተደበቀ የብዙት ንፍሬት ሆነባት። የኤስአይኤም ሚሲዮን አቋምም ከዚሁ የራቀ አልሆነም። ብራያን ፋርገር ሚሲዮኑ የተራመደበትን የልማት ሩጫና ያጋጠመውን መደነቃቀፍ ሲገመግሙ እንዲህ ጽፈዋል፤

. . . የልማት ፕሮግራሞች እንደሚጠበቀው ቀለል ሀመም የሆኑበት አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። የታቀዱት የልማት ግቦች ከታሰበው መድረሻ በእጅጉ መራቃቸው፥ የተመደበው ገንዘብ በብዙኖች እጅ መውደቱ፥

---

194 ዝኒከማሁ።

የአስተዳደራዊ ብቃት የታሰበውን ያህል ያለመሆኑ ለመንፈሳዊ ሕይወት አስተዋፅኦ ይሆናል ተብሎ የተገመተው ሁኔታ ወደ አልተጠበቀ አቅጣጫ መጓዙ የሚጠቀስ ነው። ቀስ በቀስም መንግሥታዊ የሆኑ ልማት ነክ ተቋማት እየተስፋፉና ይበልጥ ውጤታማ እየሆኑ መሄድ ሲጀምሩ ቀደም ሲል በቤተ ክርስቲያናትና በሚሲዮን ድርጅት ተይዘው የነበሩ ፕሮጀክቶችን ማፈናቀል ጀመሩ።[195]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሱት ዓይነት ችግሮች ቢጋረጡትም በንጹራዊ መልኩም ቢሆን የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከምታከና ውናቸው የልማት ፕሮግራሞች መካከል በከፍተኛ ውጤታማነታቸው በአርአያነት የሚጠቀሱም ሥራዎ ችም አልታጡም። በ1978 ዓ.ም የተጀመረው የውሃ ፕሮግራም፥ ከደብረ ዘይት ከተማ ጥቂት ወጣ ብሎ በኩሪፍቱ የሚገኘው የጉድፍ መጣያ የነበረው ቦታ ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ እየለማ ውብ የሕፃናት ማዕከል መሆኑ። በዚህ የኩሪፍቱ የሕፃናት መንደር ውስጥም ቁጥራቸው ሰማንያ ያህል የሚሆኑ እናትና አባት የሌላቸው ሕፃናት በእንክብካቤ ማደጋቸውና በግቢው ውስጥ የሚበቅሉት አትክልቶችና የእንግዳ ማረፊያው ቤት የራሳቸው አንዳንድ ችግሮች ቢኖርባቸውም በአብነት ሊጠቀሱ ከሚ ገባቸው በርካታ ውጤታማ ፕሮግራሞች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በወሎ ከፍለ ሀገር በወረባቦ ወረዳ በአራቱቲ ተበሌ ለሚገኘው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሐርቡ የግብርና ጣቢያ ጋር በመደጋገፍ ያስለመደችው የስኳር ድንች ዘር በአካባቢው ገበሬ «የቃለ ሕይወት ድንች» የሚል ስያሜ ተሠጥቶታል[196]

የልማትና ርዳታው ድርብ መልክ ይህንን ይምሰል እንጂ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናት ሙሉ ለሙሉ መከፈት እስከ ጀመሩበት እስከ 1980ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ገደማ ድረስ ስደተኛና ተገከራታች የመሰለችው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጨለማውን ዘመን ተራምዳ የነፃነቱ ወጋጋን መፈንጠቅ ሲጀምር ከኋላዋ ያስከተለችው የምዕመናን ቁጥር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ምዕመናን ነበሩ።

---

195 Brian Fargher. P. 309

196 ንጉሴ ዘውዴ የግል ማስታወሻ

The Resource Center
SIM International
P.O. Box 7900
Charlotte, NC 28241

የኮሚዩኒዝም ሥርዓት መፈራረስ

«. . . እጅም ሳይነካው፤ ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን ምስል . . . ፈጨው። . . . »
(ዳንኤል 2፥34)

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) በ1976 ዓ.ም. የመጨረሻው ቀናት ተወልዶ በደማቅ ሰማያዊ ካኪ ዩኒፎርም የደመቁ የፓርቲው አባልት አዲሱን ህፃን ፓርቲ አቅፈው ሲቀበሉና የፍልስፍናውን አበው (ማርክስ፥ ኤንግልስና ሌኒንን) እየመረቁ «ዋንጫ ነዎር!» ሲሉ የልዑል አምላክ ጣት የግዙለል በሚመስለው በታላቁ ዓለማቀፋዊ የኮሚዩኒዝም ቅጥር ላይ፤ «ማኔ፥ ቴቄል፥ ፉሬስ . . . » እያለች በመፃፍ ላይ ነበረች፤ *«ማኔ . . . እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆጠረው ፈፀመውም። . . . ቴቄል . . . በሚዛን ተመዘንህ ቀለህም ተገኘህ . . . ፉሬስ . . . መንግሥትህ ተከፈለ፥ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎችም ተሰጠ ማለት ነው።»* (ዳን. 5፥25–29)። ነብዩ ዳንኤል ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት እንዳየው ዓይነት ራዕይ የእግዚአብሔርም እጅ በዓለም የኮሚዩኒዝም ሥርዓት ላይ አላማውን በስውር እየፈፀመ በነበረበት ሰዓት የአኛዎቹ ኮሚኒስቶች ገና ከፍልስፍናው ጋር የጦፈ ፍቅር መጀመራቸው ነበር። በ1977 ዓ.ም የሶቪየት ጎብረት መሪ የሆኑት ሚካኤል ጎርባቾቭ ወደ ሥልጣን የመጡበት ዓመት ነበር። ሰውዬው ሥልጣን ከያዙ ማግሥት ጀምሮ የተከተሉት ፖሊሲ ከምዕራብ ሀገሮች ጋር ለስልሳ ዓመታት ገደማ ያህል ሻክሮ የቆየውን ግንኙነት በማደስ የኮሚዩኒዝምን ሥርዓት ከንቱነት ማሳየት ነበር። ይህንንም እርምጃ የወሰዱት በቀዳሚነት ለ27ኛው የፓርቲ ጉባዔተኞች የመርዶ ያህል የተደመጠውን ዜና በማብሰር ነበር፤

«የሶቭየት ኮሚዩኒስት ፓርቲ በሀገሪቱ ውስጥ ስለታዩት አፍራሽ አዝማሚያዎች ከነምክንያታቸው ለሕዝቡና ለፓርቲው በግልፅ የማቅረብ ግዴታ አለበት። . . . በጎብረተሰባችን ውስጥ የመፍዘዝ ምልክቶች ጎልተው መታየት ጀምረዋል። . . . የኮሚዩኒዝም ሥርዓት አንኮታኩቶንና ሁላችንንም ወደ ጥፋት አዘቅት ውስጥ ይዞን ከመግባቱ በፊት ፔሬስትሮይካ (ተሃድሶ) እና ግላዝናስት (ግልጽነት) የሚሉትን መፈክሮች አንስተን አጠቃላዩን ሁኔታ

ከፍፁም ውድቀት ለግዳን ከባድ ጥረት ግድረግ አለብን። . . . ይህንን ሥርዓት አሁን ካላሻሻልነው ሁላችንም ተያይዘን ጠፊ ነን።[197]

የሶቪየት ጎብረት ኮሚኒስት መሪ ጎርባቾቭ ይህንን መልዕክት ለራሳቸው የፓርቲ አባላት፥ ሕዝብና ለተቀሩት የዓለም ሕዝቦች ሲያበስሩ የኢትዮጵያው ኢሠፓ (የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፖርቲ) መሪ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ደግሞ በዚያው ዓመትና በዚያው ወር በቀጥታ ለፓርቲ አባላቱ፥ በተዘዋዋሪ ደግሞ ለሕዝቡ የሚከተለውን ድንጋጌ እያወጁ ነበር፤

እያንዳንዱ የፓርቲ አባል የንብረቱን ልክ ለፓርቲው አንዲያስመዘግብ። የምዕራቡን ዓለም ባህል ፊልም በፍፁም እንዳይመለከት። ለጋብቻና ለፍቺ ፓርቲውን እንዲያሳውቅ። <u>ግንኙ የፓርቲ አባልና ቤተሰቡ ቤተ ክርስቲያን አንዳይሄድና ሲሞትም በክርስትና ሥርዓት እንደ ግንኙ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እንዳይቀበር</u>። ወደ ግንኙውም የምዕራቡ ዓለም በግላቸው ጉዞ እንዳያደርጉ . . . መንፈሣዊነትን የሚያንጸባርቅ ዳንዳን በንግግርም ሆነ በጽሁፍ እንዳይጠቀሙ። . . .[198]

እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ለዓላማው እንዳደነደነ ሁሉ የኢትዮጵያ ኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎችንም ልብ እንዲሁ አደንድኖና አሳውሯቸው ነበር በግለት የሚተቹ ምሁራን አልጠሎም። ሕዝቡን በእህል ከማጥገብ ይልቅ በማይታይ የከህደት ተስፋ አእምሮውን ሞሉት፤ በግለት ብዙዎች በውስጣቸው ይደብኑ ነበር። ስለ ሰላም ከማውራት ይልቅ ሕዝቡን በቂምና በበቀል፥ በእርግማንና በመፈክር ምላሱን አሾሩት። የግጎበረሰቡን የከበረ እሴት አስትተው ሁሉም እኩል ነው በሚል የጅል ፈሊጥ ሞሉት። ልጆች ለወላጆቻቸው፥ ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዳይታዘዙ በጎብረተሰብ ውስጥ ከፉ የፍልስፍና መርዝ ረጩ።

ከሁሉም የከፋው ግን፤ «እግዚአብሔር የለም! ከሁሉም በላይ አብዮቱ! ተፈጥሮን በቴፕዋራችን ሥር እናደርጋለን!» በሚሉ የትምክህትና የእብሪት እምነት እንዲሞላ በግድም በውድም ሕዝቡን አስገደዱት። ጥፋት እያንኳኳ ሞት ሊይዛቸው እየጋለበ እንደሆነ ሊጠረጥሩም ሆነ ሊሰሙ አልፈለጉም።

በምሥራቅ አውሮፓ፤ በሀንጋሪ፥ በቼኮዝሎቫኪያ፥ በምሥራቅ ጀርመን፥ በፖላንድ፥ በሩሜኒያ፥ በቡልጌሪያ ወዘተ. ያሉት ኮሚኒስት

---

197 ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፤ ገጽ 227

198 ደበበ እሸቱ (ተርጓሚ)፤ ገጽ 334

መሪዎችና ሕዝቡ የጎርባቾቭን የጥፋት ደውል አድምጠው ማምለጫውን ሲፈልጉ የኢትዮጵያ መሪዎች ግን ከሥራቸው የሚንቀለቀለው እሳት ገና የሥልጣን ወንበራቸውን ለብ እያደረገው ነበር።

ጎርባቾቭ የሊሥፓን የአመራር አባላት በተለይም ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም መልዕክተኞችን በመላክና በግንባርም እንዲመጡ አርገው በማነጋገር የእስካሁኑ መንገድ ወደፊት ስለማያስኬድ ሶሻሊዝምን ማከረርና ማጥበቅ እንደማይገባና አነርሱም ከአጣብቂኝ ውስጥ ለመውጣት እየታገሉ መሆኑን፣ የአገርን አንድነትና ሀልውና ለመጠበቅ እንደዚሁም አስካሁን የተገኘውን ለማዳን የአቋም ለውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አበክረው መክረዋቸዋል።[199]

መንግሥቱ ኃ/ማርያምና የሚመሯቸው ጭማምንት ግን አብዛኞቹ ገና የተስፋውን ዳቦ በመግመጥ ላይ ስለነበሩና እግዚአብሔር የልቦናቸውን ጆሮ ዘግቶት ስለነበር ሊሠሙ ፈቃደኛ አልሆኑም። ሀገሪቱ ከዳር ዳር በተቃዋሚ ቡድኖች ጦርነት ተወጥራ ወገን እንደ ማገዶ ሲማገድ ቁጣው ከሀገሪቱ እንዲነሳ የየሃይማኖቱ ተከታዮች እንደየእምነታቸው ሥርዓት በጸሎትና በምህላ ሲጋደሉ የኮሚኒስቱ መንግሥት ግን፤ «ሃማባውያን» በየቤተ እምነቱ በጸሎት ስም የሚያደርጉትን «ውሸንብር» እንዲያቆሙ የማገጃ መመሪያዎችን ቁልቁል ያፈስ እንደነበር ያልመሸበት ታሪካችን ምስክር ነው።

ሕዝቡ አንድም በኮሚዩኒዝም ሥርዓት እየተማረረ፥ ሁለትም ከጦርነቱ ማቅ መውጣት አቅቶት እየማቀቀ፥ ሦስትም በርሃብና በቸነፈር እየተቀጣ ሲንገበገብ እየተወሳሰቡ የመጡት ሁኔታዎች ጥፋቱን በማቃረብ ላይ ነበሩ። በግንቦት 8/1981 ዓ.ም. በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደርጎ ለጥቂት ተረፉ። «አመፀኛ ያሏቸውንም በርካታ ጄኔራሎች ሞት ፈረዱባቸው። ርዕሰ ብሔሩ ከሞት በተረፉ ማግሥትም ሀገሪቱ የምትመራው ለቀቅ ባለ የኢኮኖሚ ሥርዓት *(Mixed Economy)* ስለሆነ በመንግሥት ይዞታነት ተጠናክሮ የነበረው የኢኮኖሚ ዘርፍ ለግል ባለሃብቶችም ክፍት እንደሆነ በመግለፅ መለሳለሳቸውን አሳዩ። በፓርቲውም ይዘት፥ ህልውናና ስያሜ ላይ ማሻሻያ ተደረገ። ይብስ ሁኔታዎች እየከረሩና እየጦዙ ሄዱ እንጂ እየተቀጣጠለ ያለውን የፖለቲካና የቀውስ ሰደድ ሊያቆሙት አልቻሉም።

---

199 ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፣ ገጽ 233

የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጥ ከተደረገ ከ1982 ዓ.ም. ማግሥት ጀምሮ በእግዚአብሔር አምላካችን ልዩ የማዳን ኃይል በየአካባቢው ተዘግተው የነበሩት በርካታ የቃለ ሕይወት አብያተ ክርስቲያናት በብዛት መከፈት ጀመሩ። የማንም የበላይ ሹም ትዕዛዝ ሳያስፈልግ ብዙዎች የጸሎት ቤቶች በአካባቢው ሹማምንት የቃል ትዕዛዝ ብቻ የተመለሱባቸው አካባቢዎች ብዙዎች ናቸው።

በዚያ አስጨናቂ ከፉ ዘመን ምዕመናንን ያስሩና ቤተ ክርስቲያናትን ይዘጉ የነበሩት የፖለቲካ ካድሬዎች ተስፋቸው ስለሚሸሽና የተመኩበት የኮሚዩኒዝም ሥርዓት እየተፍረከረከ በመምጣቱ ባዶነትና ብቸኝነት ተሰማቸው። እንኳን ሌላው ሕዝብ ቀርቶ የሥርዓቱ ዋነኞች እንኳን ሳይቀሩ ቁጣ እንደከበባቸው፥ ጥፋት እንደቀረበባቸው እየተረዱት መጡ። ፊታቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን ማዞርም ጀመሩ።

አስጨናቂ ግፍና መከራ እየተፈፀመባቸው የተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ፥ ያለ ሕግ ታስረው የነበሩ ክርስቲያኖች ከወህኒ እንዲወጡ የቀድሞው አሳሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሁኔታዎችን በግድ እያጣደፉ የቤተ ክርስቲያናትን መሪዎች ያቻኩሉ ነበር።

አስራኤላዊያን ከግብፅ ባርነት ፈጥነው እንዲወጡ ግብፃዊያን ራሳቸው ሕዝቡን እንዳፈጠኗቸውና እንዳስቸኳቸው (ዘፀ. 12፥33) ሁሉ በኢትዮጵያም እንዲሁ የተዘጉትን አብያተ ክርስቲያናት ከፍተው እንዲገቡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቀድሞ አሳዳጆች ተቻኩለዋል። የልማት መሪትና የቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታዎችንም እንዲጠይቁ ተጎትጉተዋል። ቤተ ክርስቲያናትም የቀረበላቸውን ግብዣ በደስታና በምሥጋና ተቀበሉት እንጂ በበቀለኝነት ስሜት አላስተናገዱትም።

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ትልቁ አርአያነታቸውና ምሣሌነታቸው የክህደቱን ዘመን መከራ ነጋ ጠባ እንዲህ ሆነን ነበር እያሉ በአዋጅ አለማስተጋባታቸው ነው። አምን ቅዱሳን ተሰቃይተዋል፥ ተሰደዋል፥ ቤተ ክርስቲያናትም ተዘግተዋል የመከራው ጽዋ ሞልቶ ገንፍሏል። ቢሆንም ግን ቤተ ክርስቲያናት ያለፈውን ዘመን፤ «. . . ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናምናለን» በማለት አለፉት እንጂ በምሬትና በሀዘን ፊታቸው አልጨፈገገም። መከራው ቤተ ክርስቲያናትንና ቅዱሳንን አጠራ እንጂ አላጠፋቸውም። አበዛቸው እንጂ አልቀነሳቸውም።

ኮሚዩኒዝም ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንና ለሌሎቹ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት እንደ ማንጠሪያ እሳት በማገልገል ውበታቸው እንዲወጣ ረድቷቸዋል።

የኮሚዩኒዝም ሥርዓት አብያተ ክርስቲያናትን ሲዘጋና ቅዱሳንን ሲያስር በአንፃሩ ደግሞ እንዲበዙና እንዲያፈሩ መንገዶችን እየከፈተ መሆኑን ብዙዎች አልተረዱትም።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ለበርካታ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቃለ መጠይቅ አድርጓል፤ «ኮሚዩኒዝም በቤተ ክርስቲያን ላይ ያሳደረው ተፅእኖ ምን ይመስላል?» የሚል። ሁሉም መሪዎች የሰጧቸው መልሶች ተመሳሳይ ነበሩ። «ኮሚዩኒዝም ቤተ ክርስቲያንን አጥርቷል። ቅዱሳንን አብዝቷል። አስፍቶናል። አሳድጎናል። መልካም ጊዜ ነበር።» እያሉ።

ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ማለት ይቻላል የደስታ ዓመት ነበር። በየቦታው የሚደመጠው ዜና፤ «በዚህ አካባቢ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት እየተከፈቱ ስለሆነ አመስግኑልን። የታሰሩት በሙሉ ተፈተዋል። ሰፊ ልማት ለመጀመር እያሰብን ስለሆነ ጸልዩልን። የተሻለ ምትክ ቦታ ስላገኘን እግዚአብሔርን አመስግኑልን ወ.ዘ.ተ.» የሚሉ ዓይነት ነበሩ። 1972 ዓ.ም. ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመከራ ዓመት የነበረውን ያህል አሥረኛው ዓመት ግን እንደዚያ አልነበረም። መዝሙረኛው እንዳለው ብዙዎች፤ « . . . ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ቢሰማሩም ሲመለሱ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው በድል እየወዘወዙ ነው።» ቤተ ክርስቲያንን፤ «እስከ መሠረትዋ ድረስ አፍርሱ፥ አፍርሱ ያሉት» አስጨናቂዎች የተቆረጠው ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ እንደ ንጉሥ ቂሮስ ለፈረሰውና ለሚጠገነው የእግዚአብሔር ቤት ቀዳሚ ተባባሪዎች በመሆን፤ «ሥራውን አፋጥኑ!» በማለትም በጎ ፈቃዳቸውን አሳይተዋል።

በአንፃሩ ደግሞ በራሳቸው በኮሚዩኒስቶቹ መሪዎች ካድሬዎች የኮሚዩኒዝምን ሥርዓት አሽናፊነት የሚያመለክቱት ምልክቶች ሁሉ መጥፋትና መወገድ የጀመሩት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው። በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጽ/ቤት ፊት ለፊት የቆመው ግዙፉ የሌኒን ምስል ስሜቱ በቁጣ በገነፈለ ሕዝብ ከሥሩ ተመንግሎ ወደቀ። ብዙ ሰዎች በምስሉ ላይ እየቆሙ በመርገጥ ጥላቻቸውን ገለጹ። በመስቀል አደባባይ ላይ በትልቁ የተሳለው የሦስቱ የኮሚዩኒዝም መሥራቾች (የማርክስ የሌኒንና የኤንግልስ) ስዕል ከተሰቀለበት እንዲወርድ ተደረገ። በየቦታው የተቀሰቱትና የተፃፉት የኮሚዩኒዝምን ሥርዓት የሚያገንኑት መፈክሮች

ሙሉ ለሙሉ ወረዱ። በየአደባባዩና በየመንግሥታዊ ተቋማት የተሰቀለው የኮሚዩኒዝም «ጀግኖች» ምስልና የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ፎቶግራፎች እየተሰበሰቡ ታጎሩ።

የኮሚዩኒዝም ሥርዓት መሠረት የሆኑት የሙያ ማኅበራትና ሕዝባዊ ማኅበራት ዋግ እንደመታው አዝመራ ጠውልገው አንገታቸውን ደፉ። ኢሠፓ የሚለውን ስም ሕዝቡ ተጠየፈው። በከህደት መጋረጃ ዓይኑ እንዲታወር ተገድዶ የነበረው ሕዝብ በተከፈቱት የጸሎት ቤቶች እየተመመ አምላኩን በነፃነት ማምለክ ጀመረ።

የፖለቲካው ሥርዓት በፈራረሰ ማግሥት የመንግሥት መዋቅርም ድጋፍ አጥቶ መንገዳገድ ጀመረ። የመንግሥት ተቃዋሚ ኃይሎች የጦርነቱ በለስ እየቀናቸው ወደ ርዕሰ መዲናዋ እየገሰገሱ የመምጣታቸው ዜና የዕለት ተዕለት ወሬ ሆነ። በመፈረካከስ ላይ የነበረው የኮሚዩኒስቱ ሥርዓትም የባለሥልጣናት ሹም ሽር ማድረጉን ቀጠለበት። አብዛኛው ሕዝብ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ እንዲታጠቅ ተደረገ። እሳት ከውስጥ፥ እሳት ከውጭ። ኢትዮጵያ ታዳጊ ፈልጋ እጅጋን ወደ አምላኳ ዘረጋች።

ሚያዝያ 12/1983 ዓ.ም. መንግሥቱ ኃ/ማርያም ለመላው ሕዝብ ልዩ ዲስኩር ያደርጋሉ ተብሎ በመታዘዙ የመንግሥት መ/ቤቶች በሙሉ እንዲዘጉ ተወሰነ። የርዕሰ ብሔሩ ንግግር በምጥ ላይ ላለችው ሀገር አንድ መፍትሔ ሳያመጣ እንደማይቀር ታምኖበት ሕዝቡ ሙሉ ቀን በመገናኛ ብዙሃን ላይ አይኑንም ጆሮውንም ተክሎ ዋለ። ውጤቱ ግን ምንም ፍሬ የሌለው ባዶ ጩኸት ብቻ ነበር። መንግሥቱ ኃይለማርያም ለረጂም ሰዓታት በንግግር ያጠፉት ጊዜ ምንም ለውጥና ፈውስ ይዞ አልመጣም። አልፎም ተርፎ፥ «እኔም ከሥልጣን አልወርድም፥ የአመራር ለውጥም አይደረግም። ለዚህ ሁሉ ጥፋት ተጠያቂው ሕዝቡ ነው።» ብለው ደመደሙ። ይህንን በተናገሩ ልክ በወሩ ግንቦት 14/1983 ዓ.ም. በሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን የተደመጠው ዜና በእጅጉ የሚገርምም የሚያስደንቅም ነበር፤

«የቀድሞው ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ግንቦት 13/1983 ዓ.ም. ከቀትር በፊት በአይሮፕላን ከሀገር የወጣው በሀገር ውስጥ የሥራ ጉብኝት የሚያደርግ በመምሰል እንደነበር የመንግሥት ምክር ቤት ቃል አቀባይ ትናንት ገለጠ። . . . መንግሥቱ ኃይለማርያም ከሀገር የወጣው በሲዳሞ አስተዳደር ክልል በብሳቴ መታደራዊ ግሠልጠኛ በሥልጠና ላይ የሚገኙትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ለመጎብኘት በሚል ሰበብ መሆኑንም ቃል አቀባዩ ገልጠ የተጓዘበት አይሮፕላንም ዳሽ 5 የተሰኘ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትንሽ አውሮፕላን እንደነበረ ቃል አቀባዩ ጨምሮ ገልጧል . . . ከዚያም

አቅጣጫውን በመቀየር ወደ ኪንያ አምርቶ ናይሮቢ ላይ አርፎ ከጥቂት ቆይታ በኋላ አይሮፕላን በመለወጥ ጉዞውን ወደ ዚምባብዌ መቀጠሉን አመልክቷል።» (የኢትዮጵያ ሬዲዮ ግንቦት 14/1983ዓ.ም.) የሚል አስደንጋጭ ዜና በሬዲዮና በመገናኛ ብዙሃን ተደመጠ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለአሥራ ስድስት ዓመታት ያህል ሥር ሰዶ ቤተ ክርስቲያናትን ሲዘጋ፥ ቅዱሳን ሲያሳድድ፥ መላውን ሕዝብ ለመከራ፥ ለስቃይ፥ ለጦርነት፥ ለስደትና ለጉስቁልና የዳረገው የኮሚዩኒዝም ሥርዓት ፈራርሶ፥ መሪውም በሽሽት ሀገር ለቆ በመውጣቱ ምክንያት ተስፋው ሁሉ በአሳዛኝ ሞፍግ (Tragedy) ትዕይንት ተጠናቀቀ። እየፈራረሰ የነበረውን መንግሥታዊ መዋቅር እንደገና ጠጋግኖ ለማቆም በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ የተቻለው ሁሉ ሙከራ ቢደረግም የኮሚዩኒስቱ ደርግ ሥርዓት ዕድሜ ሊራዘም አልቻለም።

በዚህ ሁሉ የታሪክ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር የከበረበትና ሕዝቡንም ከቁጣ የጋረደበት አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። የደርግ መንግሥት ሲፈራርስ አብዛኛው ሕዝብ መሣሪያ ታጥቆ ነበር። ከጫካ የገባው የኢህአዲግ (የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያ ግንባር) ሠራዊትም ሙሉ ትጥቅ ነበረው። ቢሆንም ግን ገባሪውና አስገባሪው ኃይላት የመሣሪያቸውን አፈሙዝ ሙሉ ለሙሉ አልከፈቱም። የተለያዩ ሰዎች የተለያየ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። የቤተ ክርስቲያናትና የጸሐፊው ጠንካራ እምነት ግን ተመሳሳይ ነው፤ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ያለውን ልዩ ዓላማ ከገለጸባቸው ዘመናት ይልቅ ይሄኛው ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል። ከግንቦት 13/1983 ዓ.ም. ጀምሮ በነበሩት ቀናት ሀገሪቱን የገዛውና የተቆጣጠረው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ከጫካ የመጣው ኃይል እንዲለዝብ፥ ተሸናፊው ሠራዊትም እጁ እንዲያዝ ያደረገው ሃያል አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ባይሆንማ የአልቂቱ መጠን የትና የት በደረሰ። የጥፋቱም አድማስ መጨረሻ በሌላው ነበር። ያ እንዳይሆን ግን እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሁለት አስከፊ ፍንዳታዎች ግንቦት 20 እና 27/1983 ዓ.ም. ከተማዋን አናወጡ። አንደኛው በጉለሌ አካባቢ የሚገኘው የሽጎሌ የጦር መሣሪያ ማከማቻ መጋዘን ሲሆን፥ ሌላኛው በንፋስ ስልክ አካባቢ የሚገኘውና የነዳጅ ግጠራቀሚያ ዴፖዎችንና የብሔራዊ የሰብል ማከማቻ ጎተራን ተጎራብቶ የተሠራው የከፍተኛ የጦር መሣሪያዎች ማከመቻ መጋዘን ነው። በተለይም የንፋስ ስልኩ አካባቢ ፍንዳታ ወደ ነዳጅ ማከማቻውና ወደ ሀገሪቱ ልዩ የእህል ጎተራ ቢጠጋ የሚፈጠረውን አሰቃቂ ትዕይንት መገመት አያዳግትም። ያ እንዳይሆን ግን ልዑል በእጁቹ መዳፍ ሕዝቡን

በመሸሸግ ሀገራቱን ከሰቀቀን አተረፋት። የሕዝቡ የዚያና ሰሞን ጩኸት ከህያው አምላክ ዙፋን ደረሰ፥ ጸሎቱና ምእላው ወደ አምላካችን አረገ።

ይህን የልዑል አምላካችንን ጣልቃ ገብነት በተመለከተ፤ «በእነዚያ ቀናት ሀገሪቱ ያለመንግሥት በፈጣሪያችን ቸርነት ልዩ ጥበቃ ተደርጎላት መቆየቷን በማስታወስ» ክርስቲያኖች ሁሉ በየዓመቱ በምሥጋና መንፈስ አምላካቸውን ማሰብ እንደሚገባቸው ለማሳሰብ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከኦርቶዶክስ፥ ከካቶሊክና ከወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት የሃይማኖት መሪዎችንና ምዕመናንን እያሰባሰበ በእነዚያ አስጨናቂ ቀናት እግዚአብሔር ሕዝቡን የታደገበትን ዕለት በማሰብና ለመጪው ትውልድ የተዓምራቱን ድንቅ ለማስተላለፍ ተነሳሽነቱን ወስዶ የድርሻውን ለመወጣት በየዓመቱ የምሥጋና የጸሎት ፕሮግራም እያዘጋጀ ዕለቱን በጽሞና እያሰበው ይገኛል።[200] ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይህንኑ ፈለግ ቢከተሉት መልካም ይሆናል።

እነሆ አርጌው ሥርዓት በአዲስ ሥርዓት ተተካ፤ ትናንት በነበር ሊዘከር ቦታውን ለዛሬ የለቀቀ ቢሆንም ያለፈው ለመጪው ትምህርት ይሁን። የነጋለት ከመሸበት ይማር። አምላኩ ታዳጊ የሆነለት ለነገም በእርሱ ተስፋ ያድርግ። ዛሬ የሚሰቀው የትናንቱን የመከራ ዘመን እያሰበ ሚዛን ይጠብቅ። የዛሬው የቤተ ክርስቲያን ዕልልታ የተገኘው በትናንቱ የቅዱሳን ዕንባና ደም ላይ በቅሎ ነው። ያ ዘመን ለበጎ እንደሆነ ሁሉ ይህም ዘመን ለበረከት፥ መፃኢው ዘመንም ለበጎ ይሁንልን። ከነብዩ ዳንኤል ጋር አምላካችንን እንዲህ እንበለውና ወደ የአምልኮ ነፃነቱ ዋዜማ ምዕራፍ እንሸጋገር፤

እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፥
እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና፤
ከእንተ በቀር ቅዱስ የለም።
አትታበዩ በኩራትም አትናገሩ፤
እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፥
እግዚአብሔር ሥራውን የሚመዝን ነውና።
ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣ።
የኃያላንን ቀስት ሰብሯል፥
ደካሞችም በኃይል ታጥቀዋል።
(ዳንኤል 2፥2-4)

---

200 አስፋው ተፈራ። ዕዳችንን እንክፈል። ያልታተመ በራሪ ወረቀት፥ ግንቦት 27/1991 ዓ.ም.